خيرة العقول المسلمة في القرن العشرين

# የ20ኛው ክፍለ ዘመን ሙስሊም ነቢባን

ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሸ−ሺንቂጢ




**ትርጉም**

ዐብዱራህማን ሰዒድ (ሜጢ)

# የ20ኛው ክ/ዘመን ሙስሊም ነቢባን

ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ

ትርጉም፡-

ዓብዱራህማን ሰዒድ (ሜጢ)

الوسطية للنشر والتوزيع
Al-Wasatiyyah Publishing

| | |
|---|---|
| ርዕስ | የ20ኛው ክ/ዘመን ሙስሊም ነቢባን |
| ደራሲ | ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ |
| ተርጓሚ | ዓብዱራህማን ሰዒድ (ሜጢ) |
| እትም | ፩ኛ እትም፤ 2020 እ.ኤ.አ |
| አሳታሚ | ወሰጢያ አሳታሚ |
| ኢሜይል | alwasatiyyapublishing@gmail.com |

«خيرة العقول المسلمة في القرن العشرين» لمحمد بن المختار الشنقيطي باللغة الأمهرية


# የ20ኛው ክ/ዘመን ሙስሊም ነቢባን


Copyright © 2020 Al-Wasatiyyah Publishing



Addis Ababa, Ethiopia.

# ማውጫ

1. ሙሐመድ ኢቅባል ........................................ 1

2. ሙሐመድ ዐብደላህ ዲራዝ ........................................ 13

3. ማሊክ ቢን ነቢ ........................................ 23

4. ኢስማዒል አል-ፋሩቂ ........................................ 33

5. ዓሊ ዒዘት ቢጎቪች ........................................ 43

6. ሙሐመድ አሰድ ........................................ 53

7. ሙሐመድ ሐሚደላህ ........................................ 70

# የፀሐፊው ማስታወሻ

بسم الله الرحمن الرحيم

*በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ በጣም ሩህሩህ በሆነው*

ይህ መፅሐፍ መጠኑ ያነሰ ግን ይዘቱ የገዘፈ ሲሆን በ20ኛው ክ/ዘመን የነበሩ ብርቅዬ አሳቢያንን ለማስተዋወቅ፣ የአስተሳሰባቸውን ፍሬዎችና ህይወታቸው የታነፀበትን መሰረት ለማሳየት ሞክሬያለሁ። በፅሑፉ ሒደት ውስጥ መደበኛ አካዳሚያዊ መንገድንና ዕውቀታዊ ንፅፅርን አልተከተልኩም። ለአንባቢው ገር ይሆንና ከከዋክብቱ የዕውቀት እንዲሁም የተግባር የሕይወት አምባ ተሞክሮ ይወሰድ ዘንድ ቀለል ባለ መልኩ አስፍሬያለሁ።

ሶስት መስፈርቶችን ተመርኩዤ በ20ኛው ክ/ዘመን ከነበሩ የኢስላም ምሁራንና አሰላሳዮች ውስጥ እነዚህን ሰባቱን መርጫለሁ። የመረጥኩባቸው መስፈርቶችም:-

- የምስራቁን (የሙስሊሙን ዓለም) እና የምዕራቡን ዕውቀት
- ሸሪዓዊ መረዳትን እና ሚዛናዊ አቋምን
- በአስተሳሰብ ስፋትና በመንፈስ ምጥቀት መሃል ሰብስቦ መያዝ ናቸው።

በሚቀጥሉት ስራና የጥናት ህትመቶች ሌሎች ነቢባንን ሰፋ ባለ መልኩ ለመፃፍ እሳቤው አለኝ። ይህች አጭር መልዕክት የኢስላማዊውን የስልጣኔ መንገድ መልሶ ለማምጣት ለሚሻው ሙስሊም ወጣት አጋዥ እንድትሆን እመኛለሁ። ፈጠን ባለ መልኩ የጉምቱዎቹን ሕይወት በጥልቀት በማየት፣ ከላቀው ከፊል እሳቤያቸው መርጦ በመጠቀም ምናልባትም በመፅሐፍቶቻቸው ውስጥ ጥለው ያለፏቸው የአስተሳሰብ እስትንፋሶች ላይ በራሱ እንዲጨምር ያነሳሳዋል። እነዚህን የዕውቀት፣ እምነትና ተግባር ከዋክብት እናውቅ ዘንድ የገጠመን አላህ አንባቢውንም ባለታሪኮቹንም እርሱ ዘንድ የክብር ስፍራ እንዲሰበስበን ጠይቀዋለሁ።

ሙሐመድ ቢን ሙኽታር አሽ- ሺንቂጢ

ቀጠር ዶሐ ሻዕባን 5፣ 1437 ዓ.ሒ/ ሜይ 2016

# 1

# ሙሐመድ ኢቅባል

(*የህንዳዊ ማንነት እና የሒጃዛዊ ልቦና ስሪት ባለቤት*)

ፈላስፋው ኢብኑ ሲና - “አላህ ሆይ በውጤት የታጀበ ዕድሜን ለምንሃለሁ።” ይል ነበር። የፈላስፋውና ገጣሚው ሙሐመድ ኢቅባል ሕይወት ይህ ዱዓ የተሳካበት ነው ማለት ይቻላል። ኢቅባል በ1877 ህንድ ፑንጃብ መቋረጫ “ሲያልኮት” የምትባል ከተማ ውስጥ እስልምናን በመቀበል አዲስ ከነበረ የሂንዱ ከበርቴ ቤተሰብ ተወለደ። ከኢስላማቸው በኋላ አባቱ ጥልቅ ኃይማኖተኛ እና ሱፊ ነበሩ።

ኢቅባል በእንግሊዝ ት/ት ቤት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተማረ። ቀጥሎም በወቅቱ የፑንጃብ ዋና ከተማ በነበረቺው ላሆር በመንግስት ኮሌጅ ውስጥ ተማረ። በእንግሊዝኛ እና የዐረብኛ ቋንቋ ችሎታ መጠቀ። በፍልስፍና ዲግሪውንና ማስተርሱን ጨረሰ። ምስራቅ ላሆር በነበረ ኮሌጅ ውስጥ የታሪክና የፖለቲካ ፍልስፍና መምህር ሆኖ ሰራ። ያኔ ነበር ህንድ ውስጥ የስነ-ፅሁፍና አስተሳሰብን ሕይወት ያንቀጠቀጡ የንጋት የግጥም ስራዎቹን ማሠራጨት የጀመረው። ወደ አውሮፓ በ1905 ተጓዘ። በእንግሊዙ ኬምብሪጅና በጀርመኑ ሙኒክ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርቱን ተከታተለ። በፍልስፍና ዶክትሬቱን ጨረሰ። በህግ ደግሞ የጠበቃነት ሰርተፊኬት አገኘ። በአጭር ጊዜ የዕውቀት ስንቅን ይዞ ወደ ህንድ በ1908 ተመለሰ።

ኢቅባል ወደ ህንድ እንደተመለሰ ጠበቃ ሆኖ መስራት ጀመረ። ሆኖም ግን በፍልስፍና እና ግጥም ላይ ያለው ተሰጥዖ ከጠበቃነት ስራው እየጎተተው መጣ። ህንድ ውስጥ የኢስላምን ህልውና ለመታደግ ከሚሰሩ ስብስቦችና ድርጅቶች ጋር ተቀላቀለ። ይህም የሆነው የህንድን ቀጣይ ጉዞና የብሪታኒያ ቅኝ አገዛዝ ከአገሪቱ የመውጣት ዜና በወሬ አድማስ ውስጥ መናፈስ በጀመረበት ወቅት ነበር።

ኢቅባል በህንድ ክፍለ አህጉር ላይ ህልውና እና ማንነታቸውን የምትጠብቅ፣ ኢስላማዊ ቅርሳቸውንና ስልጣኔያቸውን ከመጥፋት የምትከላከል ልዩ የሙስሊሞች ግዛት የመመስረትን ሐሳብ

ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበ ሰው ነበር። ሙሐመድ ዓሊ ጂናህ የሚባለውን እውቅ ፖለቲከኛ በሚለዋወጧቸው መልዕክቶች ይህን ሐሳብ ያሳመነውም እርሱ ነው። ጂናህ ሐሳቡን ወደ ተግባራዊ ፕሮግራምነት ቀየረው።

በውጤት ከተሞላ ረጅም ዕድሜ በኋላ ኢቅባል አፕሪል 21፣ 1938 ንጋት ላይ ከዚህች ምድራዊ ሕይወት ተሰናበተ። በህንድ ክፍለ አህጉር ላይ ያሰባት ኢስላማዊ ግዛት ከሞተ ጥቂት ዓመታት በኋላ በፓኪስታን መወለድ ተሳካ።

## ከአስተሳሰብ እና ግጥም ባህር

የግጥም መድብሎቹ እና የመፅሐፍት ድርሳናቱ እንደሚያሳዩት ኢቅባል የአስተሳሰብ እንዲሁም እጅግ ውብ ሐሳቦችን (ውልብታዎች) ትቶ ማለፉን ነው።

ዘጠኝ የግጥም መድብሎችን ያዘጋጀ ሲሆን 12 ሺህ የስንኝ ቤቶችን ይዘዋል። ከነዚህ ውስጥ ሰባት ሺው በፔርሺያ ቋንቋ ሲሆን አምስት ሺው ደግሞ በኡርዱኛ ናቸው። ከመድብላቱ ውስጥ “ጂናሑ ጂብሪል (የጂብሪል ክንፍ)፣ ሪሳለቱል መሽሪቅ (የምስራቅ መልዕክት)፣ ደርቡል ከሊም፣ ሃዲየቱል ሒጃዝ (የሒጃዝ ስጦታ) እና አል - አስራር ወሩሙዝ“ ይገኙበታል።

በምስራቁ እና ምዕራቡ ዓለማት ፍልስፍና ላይም ነቢብ እንደሆነ የሚገልፁ የተወሰኑ ድርሳናት አዘጋጅቷል። ከነዚህ ድርሳናት ውስጥ

ወሳኙ “ኢዓደቱ ቢናኢ ፊክረል ኢስላሚ” ወይም “Reconstruction of Islamic Thought” የተሰኘው ነው። ወደ አገርኛ ስንመልሰው “የኢስላማዊው አስተሳሰብ ዳግም ግንባታ” ይሆናል። ሌላኛው ደግሞ “ተጠውሩል ሜታፊዚያ ፊ ቢላዲ ፋሪስ” “The Development of Metaphysiscs in Persia” የተሰኘው “ተጠውሩል ፊክሪል ፊልሰፊይ ፊ ኢራን” ተብሎ ወደ ዓረብኛም ተመልሷል። የኢቅባል ሁሉም የግጥም መድበሎች ወደ ዓረብኛ ተመልሰዋል። ቁጥራቸውም ዘጠኝ ነው።

ከኢቅባል የትርጉም ስራዎች ውስጥ ምርጡ በ50ዎቹ በፓኪስታን የግብፅ አምባሳደር በነበሩት ፀሐፊ ዓብዱልወሃብ ዓዛም የተሠራው ይጠቀሳል። በተጨማሪም የአዝሃር ሸይኽ የሷዊ ሸዕላን ይገኛል። “ጀናሁ ጂብሪል”ን ደግሞ ሶሪያዊው ፀሃፊ ዙሃይር ዟዟ በሚገርም የግጥም ለዛ ተርጉሞታል። እዚህ ላይ የተወሡኑ ቤቶችን እንጠቅሳለን።

## ህንዳዊ ማንነት እና ሒጃዛዊ የልቦና ስሪት

አንድ ህንዳዊ ፀሃፊ ኢቅባልን እንደ ሞኝ ቆጥሮ እና አሹፎበት “ኢቅባል ማለት በጋንጀስ ፈሳሽ ወንዝ (ህንድ ውስጥ ያለ ወንዝ ነው) ዳርቻ ላይ ሆኖ ውሃ የጠማው ሲሆን፤ ግን ደግሞ በበረሃው ዓረቢያ ምድር ውሃን ፈላጊ ሰው ነው” ብሎ ፅፎበት ነበር። ይህ ፀሃፊ ያልተገነዘበው ነገር ቢኖር የዓረቢያ በረሃ ማለት ኢቅባል ዘንድ የሰው ልጅ በሙሉ ምሪትን የቀዳበት ምንጭ፣ የኢስላምን

ውሃ ጠጥቶ የረካበት እንደሆነ ነው። ያበረሃ ለኢቅባል የወንድነት፣ ጀግንነት እና የሞገስ አይነተኛ ምልክት መሆኑንም መርሳቱ ነው። ኢቅባል “ማንነትን ማፅደቅ” ሲል የተጣራበትን የፍልስፍና ብልጫ አመላካች ነው። ኢቅባል “ሻሂይን” በተሠኘ የግጥም ቤቱ በበረሃው ሲኮራ ስማውማ፡-

ለምድር ንዋይ ግዴለሽ ነኝ የበረሃ ፍሬ፤
ሁለቱ አንድ ላይ ናቸው በምግባር ደምስሬ።
በናፍቆት ልቡ እንደተሠለበ ንስር፤
ያስረሳኛል አፀድ መዓዛውን በቀትር።
ያፀድ ውበቱ ቢሠርቅም ልቡና፤
የበቀሉበት አፈር ምንጩ እንዴት ይረሳና።
በማንነት እጦት ከተራብኩኝ፤
ስለሌላው ለድለቢስነት ከተጣድኩኝ።
ክብሬን አጥቼ አውላላ ሜዳ ላይ
ለጠኔ ካመፅኩ ሞገሴ የት ሊታይ !።

ኢቅባል በህንድ የአስተሳሰብ አድማስ ያደገ ሰብዕና ቢሆንም፤ የምዕራቡን ዕውቀት በጥልቀት አድቅቆ የሚያውቅ ሙስሊም ቁጥሩ አናሳ በነበረበት በዚያ ጊዜ የምዕራቡንም ዕውቀት ከምንጩ ዘግኗል። ወተቱንም ጠጥቷል። በምዕራቡ ዕውቀት መምጠቁ ታዲያ የኢስላምን መልዕክት ከፍታ አይቶበታል። ሌላ አስተሳሰብ ሊወስደው እምነቱን ከፍ አድርጎለታል። ኢስላማዊውን ቅላፄ ሌላ ቅላፄ ላይበልጠው እርግጠኛ አድርጎታል። እንዲህም ይላል።

“ከተደበላለቀው ድምፅ መሃል ቅላፄው ያማረ፣
ከሙስሊሙ አዛን ውጪ የለም የተሻለ።”

ብሪታኒያ ተማሪ፣ ጀርመን ተመራማሪ በነበረበት አሊያ ደግሞ ጣሊያን ቱሪስት በሆነበት ወቅት እንኳ የኢቅባል ልቦና ሁሌም በሒጃዝ በረሃ እና ተራሮቿ ናፍቆት የተንጠለጠለ ነበር። በምስራቁም ይሁን ምዕራቡ አገራት ውስጥ ልቡን የሚሰርቅ ወይም ነቢብ የሆነውን ህሊናውን የሚሰልብ አንድም ነገር አላገኘም። የሒጃዝ መሬት ግን ሠርቃዋለች።

በእውነቱ ኢቅባል የፍቅር ሰው ነበር። ኢስላምን አፍቅሯል፣ ዓረብን ከኢስላም ታሪክና ባህል ጋር ባለው ቁርኝት የተነሳ ወዷል።

ነገር ግን ጥልቅ የሆነ ፍቅሩ የተገለጠው ከነብይነት መሬትና የራዕይ መንደርደሪያዋ ሒጃዝ ጋር ባለው ስበት ነው። እናም እርሱ ህንዳዊ ማንነትና ሒጃዛዊ ስሜት የነበረው ሰው ነበር።

ባላውለው ኖሮ ልሳኔን ለክቡሩ ሐረም
በፍቅር ነው እንጂ እኔስ ነበርኩ ዓጀም።

በሌላ ስንኝ ላይ እንዲህ ይላል፦

የሰሙት ድምፄ በክራሩ
የኔ ዓጀሙ ነው በሒጃዝ ክሩ።

ኢቅባል በዚህች ሕይወት ውስጥ እስካለ ከተከበረው የሐረም አንድ ጧፍ መሆን ህልምና ምኞቱ ነበር።

ከቀልብ አጢነህ በይን፣
ከሽይኽ አትጠይቅ ጉዳዩን፣
የአላህ ሐረም ወና ሲሆን ከቤተሰቡ፣
ካስማ ሁነው ጧፉ አንተ ላንድ ግንቡ።

አፕሪል 21፣ 1938 ከጠፊዋ ዓለም ወደ ዘውታሪዋ አኼራ ሲጓዝ የረዥም ጊዜ የሒጃዝን ፍቅር እንዲያዘ ነበር። ሞት አፋፍ ላይ ሆኖ እንኳ የሚከተሉትን ስንኞች እያለ ነበር ያለፈው፡-

ቅላፄ ውበቱ ያዜምኩት መዝሙሩ
ይመለስ ይሆን ወይ ከሒጃዝ ንስሩ?
ሕይወት አሳወቀች የጉዞውን መቅረብ
ለሚስጥሩስ ዓለም ይኖር ወይ አዲስ ቀልብ?

## በአላህ ባርነት ውስጥ ያለ ከፍታ

ኢቅባል ለሕይወት ያለውን ዕይታና ፍልስፍና በሶስት ቃላት መሡብሡብ ይቻላል። “በአላህ ባርነት ውስጥ ያለ ከፍታ” በሚሉት። ኢቅባል አንዳንድ ጊዜ ይህን እሳቤውን “የንጉሳን ግዴለሽነት” ወይም “የቻዮች ግዴለሽነት” ሲል ይገልፀዋል።“

የኢቅባል በአላህ ባርነት ውስጥ ያለ ከፍታ ፍልስፍና በሁለት ክፋዮች የተጣጣመ ነው። በኢቅባል አጠራር የመጀመሪያው “ራስን ማቅለጥ” ሁለተኛው ደግሞ “ማንነትን ማፅደቅ”

“**ራስን ማቅለጥ**” ሲባል የተፈለገው፡- ፈጣሪ ጋር ባለ ትስስር ውስጥ መተናነስ እና ያልተገደበ ተገዢነት ለማለት ነው።

“**ራስን ማፅደቅ**” ሲባል የተፈለገው ደግሞ ከፍጡራን ጋር በሚኖር ትስስር በራስ መተማመንንና ለራስ ጥሩ ግምት መቸርን ጠቋሚ ነው። “ከፍታ” የምትለው ቃል ኢቅባል ዘንድ ሌሎች ላይ የመኩራትንና የመኮፈስን የተጋነነ እሳቤ ያዘለች ወይም ደግሞ በራስ የመገረምን ስሜት የያዘች አይደለችም።

ከ “ፈጣሪ” እና “ተፈጣሪ” መኃል ያለን ትስስር ገላጭ ሐረግ ናት። ሙስሊም ሆኖ በእምነቱ “የመተማመን ኩራት” ያለው ግለሰብ በጣም ባነሰበት በዚያን ወቅት ኢቅባል በሕይወት ፍኖቱ ኢስላም የሚኮራ ምሳሌያዊ “ሰው” ነበር።

ይህም የሆነው ኢቅባል ከአላህ ውጪ ያለን ባርነት እንደ ውርደትና የበታችነት ስለቆጠረው ነው።

አንተ የአላህ ባሪያ ቀጥ በል፣
ለነፃ ኩሩ ሰው አያምርም መዘንበል፤
ለአላህ ከማደር ውጪ ከፍታን አትከጅል።

## ከልብ በመነጨ የፍቅር መንገድ ላይ

ኢቅባል እንደ ባህር የሰፋ የዕውቀት ባለቤትና የአዋቂዎች ናሙና ነበር። ሰባት ቋንቋዎችን ተምሯል። በብዙ ለየት ያሉ ችሎታዎችም የተካነ ነበር።

የኢቅባል መንፈስና ንፁህ የአስተሳሰብ ነፀብራቅ ከድርሰት ይልቅ በግጥም ስራዎቹ ጎልተው ይታያሉ። ሁለቱንም በሚገባ ቢችልም የልቡናን ቋንቋ ከሕሊና ቋንቋ አስበልጧል። ግጥም የእሳቤው ፈረስ ነበር። ምክንያቱም ግጥም ልብን ሳያስፈቅድ ወደ ልቡና ኩልል ብሎ ሰርጎ የመግባት ልዩ ተሰጥዖ አለው። አስተሳሰብ ግን ወደ ሕሊና ሲገባ ቀስ ብሎና ቀዝቀዝ ባለ መልኩ ነው። "የሎጂክ ድርቀት ከግጥም ውብ ቁርቆራ አይበረታም።" ይልም ነበር።

ኢቅባል ኢስላምን አጥብቆ የመያዝ መሰረቱ ቀዝቃዛው የአዕምሮ ዕውቀት ሳይሆን ከልብ የሆነ ፍቅር እንደሆነ ያምናል። የፍቅር ተፅዕኖ ከዕውቀት የጠለቀ ነው። ልቡና ከሕሊና የበረታ ኃይልም አለው። አንድ ሙስሊም "በአላህ ባርነት ውስጥ ወዳለው ከፍታ" ለመድረስ ኢስላምን በአዕምሮ ከማወቅ ወይም ያለፈውን የሙስሊሞች ብርሃናማ ቀናት ከማመንዠክ ባለፈ የሚያስፈልገው ነውም ይላል። የኢስላምን ምርጥ አስተምህሮቶችና እውነታዎች ከነስጋ-ወ-ደሙ በልቡና ውስጥ መቅበር እንጂ በአዕምሮ ብቻ ማወቁ በቂ አይደለም። ኢቅባል አንድም ቀን በዐቅልና ቀልብ መኃል ለመለየት ሽቶ አያውቅም። ይልቁንም ሁሌም ወደ ቀልብ ያዘነበለ ነው።

ይህን አስመልክቶ ግለሰባዊ የሕይወት ልምዱን እንዲህ ያካፍለናል:

በእሳቤው ፍኖት በቀላሉ ኢቅባል<br>ተጓዘ እስኪበቃው እስኪበስል

በፍቅር ጎዳና ሲመጣ
ልብ ተዘነበለ ምንም ሳያጣ።

የሚስጥራትና እውነታዎች ሙዳ የሆነውን ልብን እና ለውጫዊ ገፅታ መረጃ አፍላቂውን ህሊናን በልዩ ሁኔታ ባነፃፀረበት ቦታ ዛሬ ላይ ሙስሊም “ለዐይን በሽታው” የሚያስፈልገው “አርቆ የማስተዋል መድሃኒት” ነው ይላል። በአላህ ፍቅር የደመቀ የሙእሚን ልቡና የመመራት እና ቅን መንገድ ምንጭ ነው።

ይህን አስመልክቶም እነዚህን ቤቶች ብሏል፡-

መድህን ከከጀልክ ለዓይንህ በሽታ፣
ፍቱን ታገኛለህ የጥልቀት ዕይታ።
ያዋቂ ንትርክ ማዕከል ነው ህሊና፣
የጦርነት ማዕበል በሐሳብ ጎዳና።
አትቁም ተጓዝ ወደ መድረሻህ፣
በጉዞ ድካም ውስጥ ትርጉም ታገኛለህ።

ኢቅባል ዘንድ የልብ እና ፍቅር ቋንቋ የሰው ልጅ ለምድራዊ ስሜቱ ከመተናነሱ ጋር ምንም ትስስር የለውም። እንደውም ፍቅር እርሱ ዘንድ የመከበር መንትያ እና የከፍታ እኩያ ነው። ኢቅባል ጋር የነበረው ፍቅር ያ በኢብራሂም (ዐሰ) ውስጥ ጣዖታትን ወደ መሠባበር የወሠዳቸው አካላቸውን የለበሰው ፍቅር ነው።

መጠጥ አይደለም የነፃ ሰው ሽልማቱ
የደመቀ ድንኳንም በቆንጃጅቱ

ጠፊ የሆነም ጣዕም የምግቢቱ
ከደመና በላይ የማይበረው ውጤቱ።
ፍቅር ያስረሳል ቁስል
የሚስጥር ፋናን ይገልጣል

በሞገስ ካልሞትክ የቱ ነው ፍቅሩ
ነውር የሸፈነው መኖርስ ምኑ ክብሩ?

አላህ ዓረብ ባልሆነው ግን ልቡ በነብያዊቱ ሒጃዝ ምድር ፍቅር በተያዘው ለሙሐመድ ኢቅባል ይዘንለት።

# 2

# ሙሐመድ ዐብደላህ ዲራዝ

*(የክቡሩ ቁርአን አፍቃሪ)*

ታላቁ ዓሊም ዶ/ር ሙሐመድ ዓብደላህ ዲራዝ በ1894 ዓ.ል ግብፅ ውስጥ ከፍሩ ሸይኽ የተሠኘ አውራጃ ውስጥ ተወለዱ። የዕውቀትና መንፈሳዊ ጥብቅነት ባለቤት ከሆነ ቤተሠብ ውስጥ አደጉ። አባታቸው ሸይኽ ዓብደላህ ዲራዝ ከአዝሃር ጉምቱ ሊቆች አንዱ እና የኢማሙ አሽ- ሻጢቢን “ሙዋፈቃት” የተሠኘ መፅሐፍ ማብራሪያ የሰሩ ናቸው።

ዲራዝ ገና በለጋ ዕድሜያቸው ቁርአንን ሐፍዘዋል። ከዚያም የት/ት ጉዟቸውን አጠናቀው ዓለማቀፍ የምስክር ወረቀትን በ1916

አግኝተዋል። በ1928 በአዝሃር ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው አገልግለዋል። በ1936 ለሐጅ ከዋኔ ወደ ሒጃዝ ተጉዘዋል። በዚያው ዓመት ወደ ፈረንሳይ ሰርቦን ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ዕድል አግኝተው ተጓዙ። ፈረንሳይ ውስጥ 12 ዓመታትን ኖሩ።

እነዚህ ሁሉ ዓመታት ያለፉት ታዲያ የምዕራቡ ዓለም ዕውቀትና ባህል ምን እንደሆነ ከስረ-መሠረቱ ከማወቅ ጋር ነበር። ያን ባህል ታዲያ ከቁርአን የስነ- ምግባር ዕውቀትና መርሆች ጋር በተመስጦ ንፅፅር ውስጥ ያስገቡት ነበር። የጥናት ፅሁፋቸውን “አኽላቁል ቁርአን” (የቁርዓን ስነ-ምግባር) ወይም በፈረንሳይኛ “La Morale Du Koran” በሚል ሰርተው ከሰርቦን ዩኒቨርስቲ ዶክትሬታቸውን ይዘዋል። ሊዮ ማሲኒዩንና ሌፈ ብሮፌንሳል የተሠኙ እውቅ ኦሬንታሊስቶችን ያስገረመ የጥናት ስራ ነበር። በ1947/ 12/15 ነበር ዲፌንስ ያደረጉት።

ከረዥም ጊዜ የዕውቀት ጉዟቸው ሲመለሡ ዲራዝ ግብፅ ውስጥ የጉምቱ ዑለሞች ህብረት ውስጥ በ1949 አባል ሆኑ። በግብፅ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሃይማኖቶች ታሪክ፣ የቁርአን ተፍሲር እና የስነ-ምግባር ፍልስፍናን ተጋባዥ መምህር ሆነው አስተምረዋል።

በ1958 በፓኪስታኗ ላሆር ከተማ ኢስላማዊ ባህልና ዕውቀትን በተመለከተ በተዘጋጀ ኮንፈረንስ ተጋባዥ ሆነው ለመሳተፍ በተጓዙበት ነበር ታላቁ ዓሊም ወደ ጌታቸው አላህ የሁዱት። በህልፈታቸው ግብጽና ሙስሊሙ ዓለም እጅጉኑ አዝኗል።

## ሞሮኳዊ ስረ-ማንነት

የዲራዝ ቤተሠብ በህሊናዊ አስተሳሰብ በተለይ ከዓረባዊቷ ሞሮኮ ጋር ልዩ ትስስር ያለው ይመስላል። ምናልባትም ቤተሰቡ በተለምዶ ወደ ማሊኪ መዝሃብ ስለተጠጋ ይሆናል። የዶ/ር ሙሐመድ ወላጅ አባት ሸይኽ ዓብደላህ ዲራዝ ለስፔናዊው የፊቅህ ሰው አቢ ኢስሐቅ አሽ-ሻጢቢ መፅሐፍ "አል ሙዋፈቃት" ማብራሪያ ሰርተውለታል። ልጃቸው ዲራዝ ደግሞ መፅሐፉን በሚገባ ፈትሸውታል። ቀጥለውም ከሻጢቢ "አል-ኢዕቲሷም" መፅሐፍ የአስተምህሮቶች (ጥናትን) ስርተውበታል።

ሳይቋጩት ባለፉት "አል ሚዛን በይነ ሱነቲ ወል ቢድዓቲ" ብለው በሰየሙት መፅሐፋቸው የአል-ኢዕቲሳምን አስተሳሰቦች እንደ አዲስ ሊያሻሽሉት ሞክረዋል።

ዲራዝ በ20ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ አካባቢ ፈረንሳይ ውስጥ ት/ታቸውን ሲከታተሉ ከአልጄሪያዊው ፈላስፋ ማሊክ ቢን ነቢ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ነበራቸው። በሁለቱ ሰዎች መኃል የአስተሳሰብ መክብብ መመሳሰልም ነበር። በተለይ ደግሞ በቁርአን ጥናት መስክ ተሐድሶ በማድረጉ ረገድ የደረሡበት ውጤትም ተመሳሳይ ነው።

"አዝ - ዟሂረቱል - ቁርአንያ" በተሰኘው የማሊክ ቢን ነቢ መፅሐፍ መግቢያ ላይ ስለዚህ መመሳሰል ዲራዝ በግልፅ አስቀምጠዋል። የማሊክ ቢን ነቢን እና የዲራዝን "አን- ነበኡል ዐዚም ወ መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም" የሚሉ ድርሳናትን ያስተያየች አይን ይህን

በ20ኛው ክ/ዘመን የተከሰቱ የሁለት ጉምቱ ነቢባንን አስተሳሰባዊ ቀረቤታ አትስትም።

የአስተሳሰብና የማሰላሰሉ ረቂቅ ተመሳስሎሽ ትስስሩ በርትቶ ወንድማዊ ትብብርን አመጣ። የጋራ ትግልንም ወለደላቸው። ሁኔታቸውን ለአደጋ አጋለጠው። በወቅቱ ፈረንሳይ ውስጥ ተማሪና ስደተኛ ቢሆኑም ዲራዝ ዐረባዊቷ ሞሮኮ ከፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ትወጣ ዘንድ ከሚታገሉት ጋር አብረው በብርቱ ታገሉ።

## ኩሩ ነፍስ

የዲራዝ ነፍስ ኩሩ እና እምቢተኛ እንዲሁም ጥብቅ ነበረች። የተወሡኑ ባህሪያቸውን ሸይኽ ዓብደላህ አንሷሪ እንዲህ ይዘረዝሯቸዋል፡- “በጣም ፈጣን፣ በሳል፣ ቻይ፣ የተረጋጉ፣ ለሌሎች ተናናሽ፣ አደራ ጠባቂ፣ ውለታን መላሽ፣ ደፋር፣ ለዓላማ መቅደም፣ እውነት ላይ የማይደራደሩ፣ ልዝብ ተናጋሪ ባለጥሩ ባህሪ እና ለባልደረባ ምቹ ሰው ነበሩ።” ይላሉ።

ቁርአን አምቆ የያዘውን ተልዕኮ ተረድተዋል። በሚጓዙበትም ይሁን ባረፉበት ሁኔታ ሁሉ የኡማ ጭንቀት ተሸክመው ነበር። ተማሪያቸው ፕሮፌሰር ኢማም ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ ይህን አስመልክተው የሚከተለውን ፅፈዋል፡- “እርሳቸው ዘንድ ተቀምጠን ስንመለከታቸው ሁሌም በኢስላም ጉዳይ እና በሙስሊሞች ጭንቀት ውስጥ ሆነው ነው ሲብከነከኑ የምናገኛቸው።”

የርሳቸውን የነፍስ ከፍታ ለማየት አንዱ ናሙና በወቅቱ ፈረንሳይ በቅኝ ግዛቷ ስር የነበረችውን የዐረባዊቷን የሞሮኮ የነጻነት እንቅስቃሴ እዛው ወራሪዋ አገር ባሉበት በግልፅ መደገፋቸው ነው። የግብፅ አብዮት ሰዎች የአዝሃር ሸይኽ ሆነው ያገለግሉ ዘንድ ሲጠይቋቸው እሳቸው “አዝሃር ከፖለቲካ ባለስልጣናት ጥምዘዛ አካዳሚያዊ ነፃነቱን ከተሠጠ” የሚል መስፈርት አስቀመጡ። የአብዮቱ ሰዎች መስፈርቱን ውድቅ ሲያደርጉት ዲራዝም ያንን ዙፋን በተደጋጋሚ ቢለመኑበትም አልቀበልም አሉ።

## ደርዝ ጠበቅ አስተሳሰብ

ኢማም ዩሡፍ አል-ቀረዷዊ ዲራዝን እንደሰየሚቸው” የአዝሃር እና ሰርቦን ፍሬ” ናቸው። ኢስላማዊውንም ይሁን ምዕራባዊውን ዕውቀት በጥልቀት ከመሠረታዊ ምንጮቻቸው ማጥናታቸው ደርዝ-ጠበቅ ዕይታ እና የልዩ የትንታኔ ሠው ይሆኑ ዘንድ አስችሏቸዋል። ለየት የሚያደርጋቸው ደግሞ በወቅቱ የብዙዎችን ህሊና በመጥፎ ሲያወድም ከነበረው ከተወረሰ ባህል እና ከወራሪው ምዕራባዊ እሳቤ ድንበር መሃል ላይ ከፀጉር ስንጠቃ የራቁ መሆናቸው ነው።

በገዛሊ በሐኪም ቲርሚዚ እና አቢ ጣሊብ አል መኪ መንሳዊነት የተዋቡ፤ በዴካርት፣ ካንት እና በርጵሶን ፍልስፍናም የታመቁ ነበሩ። ዲራዝ ከቁርአን በተማሩት ምጡቅ አገላለጽ ላይ ተመርኩዘው ደርዝን በጠበቀ እሳቤ አድማሳቸው ከፍ፣

ትንታኔያቸው ጥልቅ፣ መረጃ አቀራረባቸው አርኪና ረቂቅ መሆኑ ልዩ አድርጓቸዋል።

## የቁርአን አፍቃሪ

ከዲራዝ ስብዕና መገለጫዎች፣ የዕውቀትና ተግባር ፋናቸው መፍለቂያው ዋና ምንጩ በቁርአን ፍቅር መክነፋቸው ነው። የቁርአን ውዴታ ልባቸውን ተቆጣጥሮ ያብከነከናቸው ነበር። ሲያነቡት እና ሲያስተነትኑት አሊያ ደግሞ ቆመው እየሰገዱበት እንጂ እስከማይታዩ ድረስ እውነተኛ የቁርአን ሰው ነበሩ። የዕውቀትና ጥናት ራዕያቸውን በቁርአን ብቻ ገድበውታል። ምሁራዊ ስራ ካበረከቱ እንኳ መሽከርከሪያና አስኳሉ ቁርአን ነው። ዲራዝ ለአላህ መፅሐፍ የነበራቸው ፍቅር እና በርሱም የልባቸው መንጠልጠል አብሯቸው ኑሯል። የቁርአንን ሐረጎች ልክ ልቡ እንደጠፋ አፍቃሪ ክትትልን ይከታተሏቸዋል። “የዕውቀት ፍሬዎች” በማለትም ይገጧቸዋል።

ዲራዝ በየቀኑ ያለምንም ድካምና መሰላቸት በትጋት ስድስት ጁዝእ ቁርአን ያነቡ ነበር። ቁርአንን እጅግ ያልቃሉ። የቁርአን ተፍሲር እያስተማሩ ሱጁደ-ቲላዋ ሲያጋጥማቸው ትምህርታቸውን ቆም አድርገው ሱጁድ ይወርዱ ነበር። ተማሪዎቻቸውን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ውዱእ ያስደርጋሉ። ወደ ላሆር ህንድ ለኢስላማዊ ኮንፈረንስ የጉዞ ባልደረባቸው የነበሩት ሸይኽ ሙሐመድ አቡ ዘህራ ስለርሳቸው እንዲህ ፅፈዋል፡-”የዲሻን ሶላት

ያሰግዱንና ሁላችንም ወደ ፍራሻችን ስንሄድ እርሳቸው ግን ወደ ሶላትና ቁርአናቸው ያቀናሉ። ቁርአን ሲቀሩ ወይም ሲሰግዱ እንጂ አታያቸውም።”

## ሚዛናዊ አቋም

ሸይኽ ዲራዝ ከሚዛናዊ ኢስላም አስተሳሰብ መሪዎች አንዱ ናቸው። አቋማቸው በኢስላማዊው አስተሳሰብ መከብብ ውስጥ ንዝረት በፈጠሩ አሻሚና መንታነት ያጠላባቸውን ጉዳዮች ባስተናገዱበት አጋጣሚ ታይቷል። እነርሱም ዐቅል እና ነቅል፣ ሱና እና ቢድዐ፣ መገደድና ምርጫ፣ ሰላምና ጦርነት፣ እውቀትና ዲን፣ ስነ-ምግባርና ህግ ወዘተ። ሁሉንም እዚህ መዘርዘር ባልችልም ዐቅልን (አዕምሮን) እና ነቅልን (አንቀጽ ገደብ መሆንን) በተመለከተ ያስቀመጡትን ለማሳየት እሞክራለሁ።

“በመልካም እና እኩይ ተግባራት መኃል መለየት መቻል ሰማያዊ ድንጋጌ ከመሆኑ በፊት የሰውን ልጅ ነፍስ ማዕከል ያደረገ ውስጣዊ ራዕይ ሲሆን መለኮታዊው ድንጋጌ ደግሞ ተፈጥሯዊ ስነ-ምግባርን ምሉዕ ያደርገዋል።” ብለው ያስቡ ነበር። ይህ ምሉዕነት ለሰው ልጅ ተፈጥሮ ግዴታ መሟላት ያለበት ነው። ምክንያቱም ከእውነትና ሰናይ ከባቢ አጋጅ ድሮች እንዲሁም ወደ አለመረጋጋትና መንገድ መሳት የሚወስድ ጨለማን ለመከላከል ይበጃል።

ከመለኮታዊ ምሪት ውጪ የሰው ልጅ ሰናይ እና እኩይን ለማወቅ ብቻ ለረዥም ጊዜ ትንቅንቅ ውስጥ ይቆያል። "ስሜትን በስሜት እንደምትገዳደረው አዕምሮንም በአዕምሮ ትገዳደረዋለህ።"

የሰው ልጅ ረዥም ታሪክ ይህን ማብቂያ የለሽ መንገላታት አሳይቶናል። ከቡዲሂዝም ድሎትን የመራቅ ልማድ ኒርቫና እስከ ግሪክ ስድና ምግባረ ብልሹ ድርጊት ድረስ ታዝበናል። እነዚህ ሁሉ የራዕይና በተፈጥሮ ውስጥ ያለው እኩይን ከሰናይ የመለየት ወጋገን፤ ለፍጡራኑ ተፈጥሯዊ ድንጋጌን የሰራውና ሰማያዊ ድንጋጌን ያወረደው አላህ እንደሻው መሆን እንዳለባቸው ምስክሮች ናቸው።

## መሪነት እና ተሐድሶ

ዲራዝ የሰሯቸው ማንኛውም አስተሳሰባዊ ስራዎች ከአንፀባራቂ የተሐድሶ ዕይታ የራቁ አይደለም። ተሐድሷቸው ግን እጅግ ጎልቶ የታየው በቁርአን ጥናታቸው ላይ ነው።

በዚህ ዘርፍ ያለምንም ማጋነን ዲራዝ የሁለት አዲስ እውቀቶችን መሰረት አኑረዋል። እነርሱም "አኽላቁል ቁርአን" እና "መስደሩል ቁርአን" ናቸው። በመጀመሪያው ዙሪያ "ዱስቱሩል አኽላቂ ፊል ቁርአን" በሁለተኛው ደግሞ "አን-ነበኡል ዐዚም ወ መድኸል ኢለል ቁርአኒል ከሪም" የተሰኙ መፅሐፍትን ፅፈዋል። ዲራዝ ከዚህ በፊት ያልተሞከረ መንገድ እየሄዱ መሆኑን ያውቁ ስለነበር በሁለቱ ዕውቀቶች ላይ መሰረታዊ ስራን በመስራት መጀመር ነበረባቸው። በእውነቱ በዘርፉ ያበረከቱት ስራ እጅግ ዋጋ ያለው ነው። የጥልቅ

እሳቤ እና ትጋት ውጤት ስለሆኑ መፅሐፍቱን ፈትሾ ካነበበ ሰው ውጪ ሊረዳ አይችልም።

በቁርአን ጥናት ላይ የዲራዝ ተሐድሶ ጎልቶ የሚታየው በተከተሉት መንገድ ነው። የኢስላም ሊቃውንት የቁርአንን መሰረታዊ አስተምህሮ የገለፁት በልሳነ-ዐረብ አገባብና ገለፃ ብቻ ነበር። ዲራዝ ግን የቁርአንን ተልዕኮ ከአመክንዮ እና ታሪክ ትንታኔያዊ ጥናት ነበር የጀመሩት። ይህ መንገድ ውርስ ከሆነው አካሄድ የተለየና አዲስ ነበር። ከትላልቅ ፍሬዎቹ ውስጥ ቁርአንን ከዐረባዊ አረዳድ ወደ ዓለማዊ አውድ አሸጋግሮታል።

የቁርአን ናፋቂና አፍቃሪውን ዶክተር ሙሐመድ ዐብደላህ ዲራዝን አላህ ይዘንላቸው።

# 3

# ማሊክ ቢን ነቢ

*(የኢስላማዊው ስልጣኔ ፈላስፋ)*

ሙስሊሙ አብሰልሳይ ማሊክ ቢን ነቢ አልጄሪያ ቁስነጢና ከተማ ውስጥ በ1905 በኑሮው መካከለኛ ከሚባል ቤተሰብ ተወለዱ። አባታቸው በተበሳ (አልጀሪያ ውስጥ ያለች ከተማ ናት) ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩ እናታቸው ዙሀይራ ደግሞ የቤት እመቤትና ሹራብ የሚሰሩ ሸማኔ ነበሩ። ቤተሰቡ ታዲያ ኃይማኖተኝነቱ ጥልቅ፣ የተብቃቃና የኩሩ ነፍሶች ስበስብ ነበር።

ማሊክ ቢን ነቢ “ሻሂዱል ቀርን” በተሰኘ ዲያሪያቸው ላይ የፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ወረራ በጀመረበት ወቅት በእብሪተኞቹ የፈረንሳይ ወታደሮች የሴት ልጆቻቸው ክብር እንዳይደፈር ሲሉ አያቶቻቸው እናታቸውን ይዘው ወደ ቱኒዚያ እንደተሰደዱ ፅፈዋል።

ማሊክ ቢን ነቢ ስለ ፈረንሳይ ቀኝ አገዛዝ ጭቆና፣ ስለ ኢስላማዊ ዐቂዳና ዐረብኛ ቋንቋ ላይ ልዩ ትኩረት መደረግ እንዳለበትና አስፈላጊነቱን የተረዱት ሴት አያታቸው ከምትነግራቸው ታሪክ ነበር።

ማሊክ ቢን ነቢ የቤተሰቡ ሁኔታ በተለይ ከ”ዛውየቱ አል-ዒሰዊያ” የሱፊያ መንገድ  እንቅስቃሴ ጋር የነበረው የጠበቀ ግንኙነት መኖር እንደ ኡማ ዳግም የማንሰራራት፣ የመሻሻል እና የተሐድሶ ሐሳቦች ላይ እጅግ እንዲጠበቡበት አደረጋቸው።

የማሊክ እናት ገና ልጅ ሳሉ ቁርአን እንዲማሩ ጉጉት ስለነበራት እጅግ ለፍታለች። ጉጉቷ ለአስተማሪ የምትከፍለው አጥታ መተኛ አልጋዋን በዋስትና አስከማስያዝ አድርሷታል። ይህ የእናት ትጋት ታዲያ በማሊክ ነፍስ ውስጥ የቁርአንን ፍቅር ላይነቀል ተከለው። “አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ” የተሰኘውን ድርሳናቸውንም በማዘጋጀትም ክቡሩን ቁርአን ከኦሬንታሊስቶች ትችትና ቅጥፈት ሊከላከሉበት ባንድራውን ተሸከሙ።

ማሊክ ቢን ነቢ የመድረሳንና በአልጄሪያ ፈረንሳይ ትምህርት ቤቶች አካዳሚ ትምህርታቸውን ጎን ለጎን በአንድ ላይ ይማሩ ነበር። አልጄሪያ ከሰይዲ አል-ጀሊስ ኢስላማዊ ኮሌጅ ተመረቁ። በፈረንሳይም የከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለው በ1935 በኢንጂነሪንግ ተመረቀ። በእውነቱ ማሊክ ቢን ነቢ በነበራቸው የጠና ንባብ ፍቅር እና ራስን የማስተማር ጥንካሬ ራሳቸውን አስተምረው ያበቁ ሰው ነበሩ። እርሳቸው ዘንድ ትልቁ የዕውቀት ምንጭ ይህም ነበር።

## በምስራቅ እና ምዕራብ መኃል

ፈላስፋችን ሰላሳ ዓመታትን ፈረንሳይ ውስጥ ከኖሩ በኋላ በ1956 ወደ ግብፅ አቀኑ። የንግግርና የብዕራቸው ቋንቋ ፈረንሳይኛ ስለነበር የዐረብኛ ቋንቋን በሚገባ አጠኑ። እዛ እያሉም ዶክተር ዐብዱሶቡር ሻሂን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ መፅሀፍቶቻቸውን በጥሩ ዐረብኛ ተረጎሙላቸው። ግብፅ እና ሻም የነበሩ ዓይናዎች ዘንድ ታወቁ። ማሊክ ቢን ነቢ ከጀማል ዐብዱናስር ጋር ጥሩ ግንኙነት ስለነበራቸው አስተዳደሩ ወርሃዊ ክፍያ መድቦላቸው ለሰባት ዓመታት ለፅሁፍና ሌክቸር ስራዎቻቸው ምቹ ጊዜን አግንኝተው ነበር።

ካይሮ በነበሩበት ወቅት የአልጄሪያ አብዮት ፈነዳ። ማሊክ ብዕራቸውን ለአብዮቱ ነጥለው ብዙ ፃፉለት። ማሊክ በ1963 ወደ አልጀሪያ ተመለሱ። በብዙ አካዳሚያዊ ስልጣኖች ላይም ሰሩ።

ከነዚህም ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት አማካሪ፣ የአልጀሪያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት እና የትምህርት ሚኒስትር ሆነው አገለገሉ። በ1967 ግን የአስተሳሰብ ስራዎቻቸውን ለመስራት በማሰብ ሙሉ በሙሉ ከመንግስት ስራ ራሳቸውን አገለሉ።

በ1973 ወደ ላይኛው ዓለም እስከሄዱበት ጊዜ ድረስ አንፀባራቂ የሆኑ ወደ ሰላሳ የሚጠጉ የአስተሳሰብ መፅሐፍት ስራዎችን ትተው ሰሩ። ሃያ የሚጠጉት የሕትመት ብርሃን አግኝቷቸዋል። ሌሎች ስራዎቻቸው ግን እስካሁን ሳይሰራጩ አሉ። ከእውቅና አስፈላጊ ስራዎቻቸው ውስጥ “አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ”፣ “ወዊጅሐቱል ዓለመል ኢስላሚ” ተጠቃሽ ናቸው።

## ሞገደኛ እና አዛኝ

ግብፅ ውስጥ ከማሊክ ቢን ነቢ ጋር አንድ ቤት አንድ ላይ አብረው የኖሩት ዶክተር ዐብዱሰላም አል-ሂራስ ስለ ማሊክ ሲናገሩ በሕይወቱ እና ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት እጅግ ተናናሽ እንዲሁም ቀለል ያለ ሰው ነው እንደሆኑ ይመሰክራሉ።

“ማሊክ ቢን ነቢ ከእኛ ጋር እጅግ ቀለል ብሎ ነበር የሚኖረው። ከመፅሐፍቱ ስራ ክፍያ ሲያገኝ የቤት ወጪ ክፍያ ድርሻውን ይከፍላል። ከፊላችን ከፊሉን እንደሚንተሳሰበው እርሱንም እንተሳሰበዋለን። ምንም የበታችነትና ማነስ ሳይሰማው እኛኑ ይመሳሰል ነበር” ብለዋል።

እንዲህም ሆኖ ማሊክ ቢን ነቢ ለተሸከሙት ዕውቀትና አስተሳሰብ ዋጋ የሚሰጡ የእምቢተኛ እንዲሁም ኩሩ ነፍስ ባለቤት ነበሩ። አልፎ አልፎ ጓደኞቻቸው እስኪበርድላቸው የሚጠነቀቁላቸው ከባድ ንዴትም ነበረባቸው። ቁጣ ላይ ካልሆኑ ግን ከንፋቸውን ዝቅ አድራጊ፣ የልብ ወዳጅ እና የባልደረቦቻቸውን ውለታ መላሽ ነበሩ። ሂራስ እንዲህ ይላሉ፡-"ካይሮ ውስጥ ትምህርቴን እንደጨረስኩና ወደ ሞሮኮ ለመመለስ የወሰንኩ ጊዜ ማሊክ ኢብኑ ነቢ ቤት ውስጥ ብሰናበተውም አምቢ አለኝ። በጣም የምኮራው ታዲያ ማሊክ እስከ ፖርት ሰዒድ በር ድረስ ነበር ሸኝቶ የተሰናበተኝ።"ይላሉ።

## የተሐድሶ መንገድ አብሪ

የማሊክ ቢን ነቢን የተሐድሶ ጥረቶች በሁለት ዘርፎች አጠቃሎ ማየት ይቻላል።

1) የቁርአን ጥናት ዘርፍ እና
2) የተሐድሶ አስተሳሰብ ዘርፍ

በቁርአን ጥናት ዘርፍ ማሊክ በ"አዝ-ዟሂረቱል ቁርአኒያ" ለቁርአን ከቋንቋዊ ትንታኔና ገለፃ ብቻ ይልቅ የአመክንዮአዊና የታሪካዊ ትንታኔን መሰረት ያደረገ አዲስ መንገድ አኑረዋል። ከዶክተር ዲራዝ ጋር ጎን ለጎን ስለሰሩትም መቅድሙን ጽፈውላቸዋል። እዚህ ላይ ልዩ ትኩረት የምንሰጠው አብዛሃኛው ስራቸው በተሐድሶ ዘርፍ መሆኑን ነው።

ማሊክ ቢን ነቢ ዘመናዊውን ኢስላማዊ አስተሳሰብ በማደሱ ዙሪያ የከበረ አስተዋፅዖ አድርገዋል። በ19ኛው ክፍለዘመን መቋጫ አካባቢ የተነሱ የተሐድሶ አንቅስቃሴዎች እንደመነሻ ያደረጉትን የአስተሳሰብ ምንጭም ሲያፀዱ ነበር። ማሊክ ቢን ነቢ የቀረፁዋቸው የገለፃ ቃላት በሁሉም ልሳን ላይ የተለመዱ ሆነዋል። ለምሳሌ "ቅኝ አገዛዝ" እና "የቅኝ አገዛዝ ትይዩ"፤ በ "ሙት አስተሳሰብ" እና "ገዳይ አስተሳሰብ" መኃል ያለውን ትስስር፣ የኢስላማዊውን ስልጣኔ የዕድገት እርከኖች "የመንፈስ/ ከፍታ፣ ቀጥሎ የሕሊና/ የመስፋት እና ስሜት/ ውድቀት በማለት የገለፁበት መንገድ አዲስ ነበር ።

ማሊክ ቢን ነቢ የሙስሊሙ ማህበረሰብ መሰረታዊ ችግርና ተግዳሮት የ"ስርዓት ጠበቅ" አሰራር አለመኖር እንዲሁም የተሐድሶ ተግዳሮት እንደሆኑ ደርሰውበታል። ማህበረሰብ ተኮር ለውጥ ይመጣ ዘንድ በመላ ምት ተግባራዊ መርሆችን በግልፅ ተናግረዋል።

ማሊክ ቢን ነቢ በሙስሊሙ ዓለም በ20ኛው ክፍለዘመን መባቻ የተነሱ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች በዐቂዳ ርዕስ ላይ እንዳለፈው ዘመን ምሁራዊ ትንታኔ ውስጥ ብቻ መዘፈቃቸውን አስተውለዋል።

ማሊክ እንደሚሉት እነዚህ እንቅስቀሴዎች ተልዕኳቸውንና ታሪካዊ ሚናቸውን አጥተዋል።

ምክንያቱም "አንድ ሙስሊም ዐቂዳውን በዘፈቀደ አይለቅም፣ ምክንያቱም አማኝ ሆኖ ቆይቷል። ግን ዐቂዳው ከሁነኛ ኃይሏ

ተራቁታለች። ምክንያቱም ማህበረሰባዊ ብርሃኗን አጥታለች። ችግሩ ታዲያ እርሱ ስለሚይዛት ሳይሆን ማስተማር ያለብን እጅግ አስፈላጊው ነገር እርሱ ዘንድ ያለቺውን ዐቂዳ ማንቀሳቀስና አዎንታዊ ኃይሏን እንዲሁም ማህበራዊ ተፅዕኖዋን መመለስ ነው የሚኖርብን። በአንዲት አገላለፅ ችግራችን ለሙስሊም ስለአላህ መኖር በምንገልጠው ልክ መኖሩን በጥልቅ ስሜት ውስጥ እንዲኖረው ማስቻል አለመቻላችን ነው።” ይላሉ።

## የሰውን ልጅ ውስጥ መቀየር

ማሊክ ቢን ነቢ የሸይኽ ሙሐመድ ዓብዶን እና የሙሐመድ ኢቅባልን የአስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች አነፃፅረው ልዩነታቸው ላይ ደርሰዋል። የመጀመሪያው ኢስላማዊ ተግዳሮቶችን አዕምሮን በመጠቀምና ፅንሰ-ሐሳብ ተኮር በሆነ መልኩ ብቻ ለማስተካከል የሚጥር፣ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የሰውን ልጅ ውስጥ እንዲሁም ማህበራዊ ከባቢውን መቀየር ግብ አድርጎ የሚሰራ የተግባር መዝሐብ ሆነው አግኝተዋቸዋል። ማሊክ ይህን አስመልክተው “በሸይኽ ሙሐመድ ዓብዶ የሚመራው የተሐድሶ ትምህርት ቤት ንድፈ-ሐሳቦች ላይ ብቻ ያተኮረ ስርዓት ነው። ኢቅባል ደግሞ ስለ አላህ ማወቅ ብቻ ሳይሆን የሚፈለገው ሰፊና ረቂቅ በሆነ ትርጉሙ ከአላህ ጋር ያለንን ቅርበት በመግለፅ መገናኘት ነው። የሚፈለገው ቋንቋዊ ግንዛቤ ብቻ ሳይሆን ለዘውታሪው እውነታ መገለጥ ነው።” ሲል ፅፈዋል።

በማሊክ አገላለፅ ታዲያ በሸይኽ ሙሐመድ ዓብዶ የሚመራው የተሐድሶ ትምህርት ቤት “ከትጉኃን ተጣሪዎች ይልቅ አስደማሚ ባለሙያዎችን (ተናጋሪዎችን) ሲያስመርቅ ነው የቆየው።” አስደማሚው ባለሙያ ምንም ጭንቀትና ተልዕኮ ሳይሸከም ከተግባር ይልቅ የክርክር ማገዶን አቀባይ ነው።

ማሊክ ቢን ነቢ የተሐድሶ አስተሳሰብ ከነስፋቱ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ግዙፍ አዎንታዊ ተፅዕኖ ማሳደር ይችል ነበር ባይ ናቸው። “ሸይኽ ሙሐመድ ዓብዶ የተጓዙበትን የ”ኡሱል” እሳቤ እና ጀማሉዲን አል አፍጋኒ ያስቀመጡትን ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ እይታዎች አንድ ላይ ማስኬድ፣ ንድፈ-ሐሳባዊ እሳቤዋን ማደርጀት ብትችል ኖሮ ጉዳዩ ዐቂዳን ከማደስ ወደ ተሻገረ መንገድ አድራሽ ነበር።” ይላሉ።

ኢቅባል “ያመነች ነፍስ ቁርአንን አስተንትኖ ማንበብና ወደ ተግባራዊነቱ ካልወሰዳት፣ ጣዕሙን ካልቀመሰችው ማነብነቡ እንዲሁም በርሱ መከራከሩ አይጠቅማትም” በሚለው ሐሳቡ ማሊክ ቢን ነቢን ቀድሞታል።

ኢቅባልና ማሊክ በተጨማሪም ሌሎች የሙስሊሙ ዓለም ነቢባን የተስማሙበትን  በሽታን የመለየት ስራ (ዒልመል-ከላምን ለማለት ነው) የኢስላማዊውን ችግር ከመሰረቱ ፎርጂድ ያደርገዋል።

ማሊክ እንደሚሉት የሙስሊሞች ታሪካዊ ተጨባጭ እንደሚያሳየው “ተከራካሪዎች የሚፈልጉት ማስረጃ እንጂ እውነታን

አይደለም።” ለዚያም ነው “ዒልመል ከላም የዲንን ማህበሰባዊ ችግር የመፍታት ሁነኛ ሚና አይወጣም።” ያሉት።

ዛሬ ላይ የሙስሊሙ ማህበረሰብ እንደሚታወቀው የኪሳራ ማዕከል ነው። ይባስ ታዲያ ያንኑ ለመመለስ ዘመናዊ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች እዚያም እዚህም ተወልደዋል። በዕውቀት ዘርፍ መቋጫ በለላቸውና የስራ ውጤት በማይጠበቅባቸው የሩቅ ሚስጥራት ዙሪያ ሰዎችን በክርክር ጊዜያቸውን የሚይዙ ናቸው።

የኢስላማዊውን ስልጣኔ ፈላስፋ ማሊክ ቢን ነቢን አላህ ይዘላቸውለት።

# 4

# ኢስማዒል አል-ፋሩቂ

*(በምዕራቡ ዓለም የምስራቁ ጭንቀት ተሸካሚ)*

ዶክተር ኢስማዒል ራጂ አል-ፋሩቂ በፍልስጤሟ ያፋ ከተማ ውስጥ በ1921 ዓ.ል ተወለዱ። ኢስላማዊ ትምህርታቸውን በመስጂድ መድረሳና ቤት ውስጥ የሸሪዓ ዳኛ ከነበሩት አባታቸው ላይ በመማር ጀመሩ። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዲሞኒሺያን ፍራንስ ትምህርት ቤት ተከታተሉ። እኤአ በ1941 በቤሩት ከሚገኝ የአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ በፍልስፍና ዲፓርትመንት ዲግሪያቸውን ያዙ።

ወራሪዋ ፅዮናዊት አገር እስከተወለደችበትና እርሳቸውም ወደ ተቃውሞ እስከገቡበት ጊዜ ድረስ በእንግሊዝ ውክልና ስር በጀሊል አውራጃ ከንቲባ ሆነው አገልግለዋል። ወደ አሜሪካ ተጉዘውም በኃይማኖቶች ፍልስፍና ላይ ሁለት የማስተርስ ጥናቶችን ሰርተዋል። የመጀመሪያው በ1949 ከኢንዲያና ዩኒቨርሲቲ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ1951 ከሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ነበር። በ1952 ከኢንዲያና ዩኒቨርሲቲ ዶክትሬታቸውንም ጨርሰዋል።

በምዕራቡ ዓለም ሳሉ ፍልስፍናን፣ የአይሁድን እና ክርስትና እምነቶችን ታሪክና አስተምህሮ አሜሪካ ውስጥ በብቃት ከተማሩ በኋላ ፋሩቂ እምነታቸው ኢስላምን ደግሞ በጥልቀት የማወቅን ሐሳብ ይዘው ወደ ግብፅ ተጓዙ።

ከ1954-1958 ድረስ አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ለ4 ዓመታት ተማሩ። ጥልቅ ኢስላማዊ ዕውቀትንም ገነቡ።

ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ዳግም ወደ ምዕራቡ ዓለም በመመለስ በካናዳ ማክጊል ዩኒቨርሲቲ የማስተማር እና የምርምር ስራቸውን ጀመሩ።

ፋሩቂ በ1961 ወደ ፓኪስታን ካራቺ ኢስላማዊ የጥናት ማዕከልን ለመመስረት ተጉዘዋል። ከዚያም ከ1963-64 በቺካጎ ዩኒቨርሲቲ ከ1964-68 ሲራኪዩዝ ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው ዳግም ወደ አሜሪካ ተመለሱ። ቀጥለው ከ1968 ጀምሮ ሰማዕት እስከሆኑበት

ዓመት 1986 ድረስ ለ18 ዓመታት በቴምፐል ዩኒቨርሲቲ ነበር ያሳለፉት።

## የሴራ ሰለባው አምባሳደር

ከቀደምት ንጉሳን ልማድ ውስጥ በመካከላቸው መልዕክት አመላላሽ የሆኑ አምባሳደሮቻቸውን አለመግደል አንዱ ነበር። ይህን ፖለቲካዊ ባህል የክብርና ሞገስ ምልክት አድርገው ይቆጥሩታል። ነገርግን ወደ ክርስትያኑ ምዕራቡ ዓለም የምስራቁ ኢስላማዊ ዓለም አምባሳደር የነበሩት ኢስማዒል አል-ፋሩቂ በክህደትና ሴራ ተገደሉ። ፋሩቂ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ የበደል ክስ ይዘው ነበር የመጡት። ሆኖም ምዕራቡ በክርስትና ቦታ የእስራኤልን አምልኮ ተክቶና በደልን መሸጎ እየጠበቃቸው ነበር። በሒጅራ አቆጣጠር 1406 ረመዷን 18ኛው ለሊት ወይም እኤአ 1986 ሜይ 27 ኢስማዒል አል-ፋሩቂ እና ባለቤታቸው ዶክተር ሊሚያእ አል-ፋሩቂ በስለት ተወጋግተው ተገደሉ። ባለቤታቸው ሊሚያእም የስነ-ጥበብና ስነ-ሕንፃ ልምድ ያላቸው ባለሙያና አዋቂ ነበሩ።

ይህ ሁሉ የደረሰባቸው ታዲያ የፍልስጤም ምድርንና የሕዝባቸውን ጉዳይ ነክሰው ስለያዙ፣ በያዙት ጠንካራ አቋም እና በአሜሪካ ማህበረሰብ ውስጥ ኢስላምንና ባህሉን ለማስፋፋት ምንም ሳይደክሙ በዳዕዋ ስራ መጠመዳቸው እንዲሁም የሰው ልጅ ፀር የሆነውንና ዘረኛውን የፅዮኒዝም አስተሳሰብ በመረጃ ከስር መሰረቱ ራቁቱን በማስቀረታቸው የተነሳ ነበር። የፋሩቂ አስተሳሰብ

አልሞተም። እንዲያውም እርሳቸው የተጓዙበት እውነትን አምባገነን ፊት የመናገር መንገድ ለትውልድ ስንቅን አስቋጠረ።

## አውደ ጥበባዊ አዋቂ

ፋሩቂ በፍልስፍና፣ ታሪክ እና በሌሎች የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች የታጨቀ ተምሳሌታዊ ሙስሊም ልሂቅ ነበሩ። ዐረብኛ፣ ፈረንሳይኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች እንደ አፍ መፍቻ ይቀላቸው ስለነበር በሶስቱም ይጽፋሉ ይናገራሉም።

ዶክተር ጀማል በርዘንጂ በ1972 አንድ ምሽት ቤታቸው ፋሩቂን ራት ጋብዘዋቸው ነበር። እንግዳው ለአንድ ሰዐት ያህል በተለያዩ እምነት ተከታዮች ፊት ንግግር አቀረቡ። በንግግሩ መጨረሻ ላይ አንድ ቄስ አስተያየት ለመስጠት እጃቸውን አወጡና “በርግጥ በዚህች ምሽት ብቻ ስለ ክርስትና ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ያልተማርኩትን ተምሬያለሁ።” አሉ።

ፋሩቂ ለየት ያሉ የአስተሳሰብ ድልቦችን ትተው አልፈዋል። ከዚያም ውስጥ 25 መጽሐፍትን፣ ከመቶ በላይ ጥናቶችንና የአካዳሚ አርቲክሎች ይገኙበታል። አብዛሃኛው ስራዎቻቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ናቸው። በእውነቱ ፋሩቂ የሙስሊሙን ሕሊና ነጻ ለማውጣትና ኢስላማዊውን አስተሳሰብ ለማደስ ልዩ አስተዋፅዖ ነው ያበረከቱት። በኃይማኖቶች ጥናት አስተምህሮታቸው ብዙ የዕውቀት ልሂቃን በእጃቸው እንደተመረቁ ሁሉ ውስን

መፅሐፍቶቻቸውም ወደ ዐረብኛ ተተርጉመዋል። ከነዚያም ውስጥ አንዱ “የኢስላማዊው ስልጣኔ አትላስ” ተጠቃሽ ነው።

ፋሩቂ ያበረከቷቸውን የተሐድሶ አስተዋፅዖዎች በአራት ማዕከላት ማጠቃለል ይቻላል።

1) ኢስላማዊ ስልጣኔ
2) ኃይማኖታዊ ንፅፅር
3) ዕውቀትን ማስለም እና
4) የፅዮናዊነት ዕውነታ

## ኢስላማዊ ስልጣኔ

በዚህ ዘርፍ ፋሩቂ እና ባለቤታቸው ሊሚያእ የፃፉት አንፀባራቂና ግዙፍ አስተዋፅዖ አላቸው። እርሱም “የኢስላማዊው ስልጣኔ አትላስ” ነው። መቅድሙን እንደሰሩት ዶክተር ሒሻም አጥ-ጣሊብ አገላለፅ ይህ መጽሐፍ “የቲም ሆኖ የተወለደ” መፅሐፍ ነው።

ምክንያቱም በሕትመት እርከን ላይ እያለ ነበር ዶክተር ፋሩቂ እና ባለቤታቸው ሊሚያእ ሰማዕት የሆኑት። የአላህ (ሱወ) ፀጋ ሆነና መፅሃፉ ለነርሱ ምስክር፣ ለትግልና ጥረታቸው መስካሪ ሆኖ ወጣ። በሕይወታቸው የብስለትና ስክነት እርከን ላይ በደረሱበት የሰሩት የእሳቤያቸው ውጤት ነው። ምናልባትም የዚህ መፅሃፍ መውጣት ይሆናል ብሩወይዝ መንሱር ዜና እረፍታቸውን አስመልክቶ

በዘገበበት “የአዋቂ ብዕር ከሴረኛና ከሃዲ ስለት ይጠነክራል።” ብሎ እንዲጽፍ ያደረገው።

ይህ መፅሐፍ በዕይታ አድማሱ ከጊዜና ቦታ አናት በላይ መርዘሙ ይለየዋል። ፋሩቂ በኃይማኖቶች ታሪክ ጥናት በተለይ አይሁድና ክርስትና ላይ የነበራቸው የሰፋ ዕውቀት፤ ሊሚያእ ደግሞ በኢስላማዊ ስነ-ጥበብና ስነ-ህንፃ ያካበተቺው የጠለቀ ልምድ በዚህ ዘርፍ ከተሰሩ መፅሃፍት የኢስላማዊውን ስልጣኔ ገፅታ በተለየ መልኩ እንዲያቀርቡት አድርጓቸዋል። ፀሐፊያኑ አዲስ የአፃፃፍ ዘዬንም ተከትለዋል።

የመፅሀፉን ይዘትም በተመለከተ የስልጣኔውን ውልደት የወቅቱን ተጨባጭ፣ በዙሪያው የሚሽከረከርበት አስኳሉን ተውሒድ፣ ራሱን የገለፀበትን ቅርፅ እና ጎልቶ መታያ መልኩን አብራርተውበታል።

## ኃይማኖታዊ ንፅፅር

ፋሩቂ በኃይማኖት ንፅፅር ጥናት ዘርፍ “የዓለም እምነቶች ታሪካዊ አትላስ” በሚል ርዕስ ድርሰት ሲኖራቸው በዚሁ ድርሳን ውስጥ ለኢስላም ልዩ ክፍል ሰጥተው ገለፃው የሚስብ መግቢያ አዘጋጅተውለታል። የኢስላምን የተልዕኮ ልዕልና፣ ከሌሎች እምነቶች አንፃር ያለውን ከፍታ፣ የቀደሙ ሰማያዊ መልዕክቶችን ጠቅሎ የያዘ እንዲሁም አዕምሮና አምክንዮ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን አብራርተዋል።

በተጨማሪም “አኽላቁል መሲሒያ” በሚል ባዘጋጁት ድርሳን ደግሞ ክርስትናን ከመጀመሪያ ምንጩ አንፃር በንድፈ-ሐሳብና ታሪክ መሰረት ተችተውበታል። መፅሐፉን ያዘጋጁበት ማክጂል ዩኒቨርሲቲ የነበሩ ብዙ ቀሳውስት የአንባቢ ክርስትያኖችን እምነት ያርዳል በሚል መፅሐፉ እንዳይሰራጭ ለመከላከል ሞክረው ነበር። ፋሩቂ በዚህ ዘርፍ አያሌ ድርሳን አላቸው።

## ዕውቀትን ማስለም

በሙስሊሞች የዕውቀትና ባህል ጉዞ ውስጥ ዘመናዊ፣ ሰብዐዊና ማህበራዊ ሳይንስ ዕውቀት ዘርፎች ኢስላማዊ ቅርፅ እንዲይዙ መሰረታዊ አስተያየቶችን አኑረዋል። ፋሩቂ ይህን ያሉበት ምክንያት እነዚህን ሳይንሶች ሙስሊም አዋቂ በአዎንታዊ መንገድ የሚጠቀምበት አጋዥ እንጂ ማንነቱን፣ እምነቱንና በራስ መተማመኑን የሚሰልበው ማዕበል መሆን የለበትም ከሚል መከራከሪያ ነው።

ፋሩቂ የዘመኑን ሙስሊም የአስተሳሰብና ትምህርት ስርዐት ህመሙን ለይተውታል። እንዲሁም በባህሉ ውስጥ የአንቀሳቃሽ ኃይሉን አለመኖር አውቀዋል። የልማዳዊ እምነት አስተምህሮት እና የዘመናዊ ትምህርት መቀላቀልን ኮንነዋል።

ይህ አካሄድ በቅድመ አያቶች መንገድ ብቻ የታወረ ወይም በእምነትና ባህል ስርዓቱ ኋላ ቀር በሆነው የምዕራቡን ዓለም ጭፍን ተከታይ የሚያፈራ እና ያልረጋ ስብዕናን ወላጅ ነው።

በኢስላማዊ ጥናት ራሳቸውን ያበቁ ልሂቃን ደግሞ ማንነታቸውን ያበለፅጉ፣ የእይታ ችሎታቸውን ይገነቡ እና ጊዜው በደረሰበት ቋንቋ ያወሩ ዘንድ በሂውማን ሳይነስም ጥልቅ እውቀት ይኖራቸው ዘንድ ይከጀላል። ፋሩቂ ከዶክተር ዓብዱልሐሚድ አቡ ሱለይማን ጋር በመሆን ዛሬ ድረስ ሙስሊሞች የሚያስፈልጋቸውን የተደራጀ International Institute of Islamic Thought (IIIT) ወይም ዓለማቀፍ የኢስላማዊ አስተሳሰብ ማዕከል መስርተዋል።

## የፅዮናዊነት ዕውነታ

ፋሩቂ የፅዮኒዝምን እውነታ በማሳወቁ ዘርፍ ሶስት መፅሐፍትን አበርክተዋል።

- ኢስላምና የአስራኤል ችግር
- በአይሁድ እምነት የፅዮኒዝም ስረ-መሰረት እና
- የአይሁድ እምነት ሴክታሪያን ናቸው።

ስራቸው በጥልቅ ይዘቱና በትኩረት አቅጣጫው የተለየ ከመሆኑ ጋር አንባቢ የበደል ህመምም ይሰማዋል። ፋሩቂ በአይሁድ እምነትና የምዕራቡ ዓለም ስልጣኔ ዕድገት የጠለቀ እውቀት ነበራቸው። ፅዮኒዝምን በሚገባ ከገለፁ በኋላ ዛሬ ላይ ሙስሊሞች በዋነኛ ጠላታቸው ላይ የግንዛቤ እጥረት እንዳለባቸውም ፅፈዋል። እስራኤልን እንደ የምዕራቡ ዓለም ቅኝ አገዛዝ ወይም የተደጋጋሚው መስቀል ጦረኞች አንድ መገለጫ አድርገው

እንደሚያስቡና ያም ስህተት እንደሆነ አበክረው ተናግረዋል። እርሷ ግን ከዚህ የላቀችና ጠንቃቸው ናት።

የእስራኤል መወለድ ሶስት የአስተሳሰብ እርከኖችን አልፎ የመጣ እንደሆነ አብራርተዋል።

1) በክርስትና የኃጢአት ውርስ ከትውልድ ትውልድ መተላለፍ ቲዎሪ
2) የአይሁዶች እኩልነትን ያልተቀበለውና ቃሉን ያጠፈው የአውሮፓ ብርሃናማ ወቅትና
3) በአይሁድ እምነት የዘር ማዕከል ናቸው

ለዚህ ነው አይሁድ ይህን ሁሉ (በአውሮፓውያኑ) የመገፋትን ቁስል ተሸክሞ ስሩን ከአውሮፓ ነቅሎ በፍልስጤም ምድር የተዘራው። እውነታው ግን ይህን ያደረገው ዘግይቶና የግብር ይውጣ፣ የአጣብቂኝ ጊዜያዊ እንጂ የመጨረሻ መፍትሄ አይደለም። የምዕራቡ ክርስትና ስር ጠለቅ ችግር ወደ ታሪክ መድረክ ዳግም እየመጣ ባለ ግዙፍ ሙስሊም ኡማ ሒሳብ ውስጥ የማይጣጣ የራሱ እዳ ነው።

በምዕራቡ ዓለም የምስራቁን ሐሳብ ተሸካሚ ኢስማዒል ፋሩቂን አላህ ይዘንላቸው።

# 5

# ዓሊ ዒዘት ቢጎቪች

*(በሰብዓዊነት አድማስ ውስጥ ያለፈ ኢስላሚስት)*

ፐለቲከኛውና አሰላሳዩ ዓሊ ዒዘት ቢጎቪች በ1925 ሰሜን ምዕራብ ቦስኒያ  ቡሳና ክሩባ በምትሰኝ አውራጃ ባልካን ውስጥ በኢስላም ታሪክ ስር ካለው ቤተሰብ ተወለዱ። እናታቸው እጅግ ሲበዛ ጥንቁቅና ጥብቅ ስለነበሩ በልጃቸው ልብ ውስጥ የኢስላምን ፍቅር ተከሉ። ዓሊ ገና በልጅነታቸው የቁርአን በተለይ ደግሞ የሱረቱ-ረህማን አፍቃሪ ሆኑ።

ወጣት ሆነው ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳሉ “የሙስሊም ወጣቶች ሕብረትን” መሰረቱ። ሕብረቱ ከዚህ በኋላ ሰፍቶ ወደ እውቀትና

በጎ አድራጎት ድርጅትነት አደገ። በድርጅቱ ዓሊ ዒዘት ሕግ ካጠኑበት የሳራጀቮ ዩኒቨርሲቲ አያሌ ተማሪዎች ተሳቡበት። ድርጅቱ በ2ኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ግዙፍ ማህበራዊ ግልጋሎት አበርክቷል።

የጀርመን ፋሺስት ስርዓት የዩጎዝላቪያን ግዛት በወረረበት ጊዜ ይህቺን የወጣቶች ማህበር ህጋዊ አካልነትን ነጠቃት። ዓሊ ዒዘት ጠበቃ ሆነው ተመረቁ። መሰረታዊ የአውሮፓ ቋንቋዎችን በተለይ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና እንግሊዝኛን በተሟላ መንገድ ለማወቅ ጥረት አደረጉ። በተመሳሳይ በግል ጥረታቸው በማሕበራዊ፣ ስነ-ፅሁፍ እና ኢስላማዊ አስተሳሰብ ዕውቀት የጠለቀ ኃብት አካብተዋል።

በነዚህ ዘርፎች ምጡቅ ለመሆናቸው በተለይ “ኢስላም በምስራቅ እና ምዕራብ መኃል (Islam between East and West)” እና “ወደ ነፃነት ሽሽቴ” የተሰኙት መፅሐፎቻቸው ምስክር ናቸው።

## የነጭ ሞገደኞች ተገዳዳሪ

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በጆሴፍ ቲቶ የሚመራው የኮሚኒስት ፓርቲ ወደ ስልጣን ሲመጣ የዩጎዝላቪያ ሙስሊሞች ፈተና ስር እየሰደደ ሄደ። ለኢስላም ጨቋኝ እና ተቃራኒ ስርዓት ስለነበር ብዛት ያላቸውን ሙስሊም መሪዎች ለእስር ዳረገ፣ ከነርሱም ብዙዎቹን ገደለ። አብዮታዊ መንገድን የሚከተለውና ግልፅ ፖለቲካዊ ቋንቋ የነበረው የሙስሊም ወጣቶች ሕብረት ላይ

የኮሚኒስቱ ስርዓት ብትር በረታበት። ስርዓቱ ዓሊ ዒዘትን ጨምሮ ሁለት ሺ የሚሆኑትን ለእስር ዳረጋቸው። ዓሊ ከ1949-1954 ድረስ ለአምስት ዓመታት በእስር ቆዩ።

ዓሊ ከእስር ከተፈቱ በኋላ በ1962 የጠበቃነት ስራቸውን ጀመሩ። የኢስላማዊ አስተሳሰብ ስራቸውን ወጥ በሆነ የፅሁፍ ስራ በዩጎዝላቪያ ሙስሊም ልሂቃን ስር ይታተም በነበረ ታከፊን በተሰኘ ጋዜጣም መስራት ቀጠሉ። በ1981 የፅሁፋቸው ስብስብ ስራ "አል-በያኑል ኢስላሚ" በተሰኘ ጥራዝ ወጥቷል። የመፅሐፉ ርዕስ "አል-በያኑል ሹዩዒ" (የኮሚዩኒዝም ምንነት) ከተሰኘው የካርል ማርክስና ፈሬድሪክ ኢንግልዝ በ1848 ከፃፉት የኮሚዩኒዝም ወንጌል ብለው ከሚያስቡት መፅሐፍ ጋር ትከሻ የሚለካካ ስለመሰላቸው በኮሚኒስቱ ባለስልጣናት ካምፕ ከፍተኛ ንዝረትን ቀሰቀሰ።

ዓሊ ዒዘት በ1983 የአስራ አራት ዓመታት ፅኑ እስራት ተፈረደባቸው። ለሁለተኛ ጊዜ በኮሚኒዝም እስር ቤት ውስጥ አሰቃቂ አምስት ዓመታትን አሳለፉ። በ1989 የኮሚኒዝምን ስርዓት መንኮታኮት ተከትሎ ፍርዳቸው ዳግም ታይቶ በነፃ ወጥተዋል። እንደ አዲስ በተከፈተው የለውጥ አድማስ ውስጥ ፖለቲካዊ ስራቸውን ጀመሩ። የፖለቲካ ፓርቲ መስርተውና ምርጫ ተወዳድረው አሸንፈው የቦስኒያን ሪፐብሊክ ከ1990 እስከ 2000 ድረስ አስተዳድረዋል። ሲታወስ የሚኖር አሻራ አኑረው በ 2003 ዓለማችንን ተሰናብተዋል።

## የአረመኔያዊው ስልጣኔ አሸናፊ

የቦስኒያ ሙስሊሞች በኮሚዩኒዝም ስርዓት መውደቅ መልካም ነገር እንደሚመጣ አስበው ነበር። ወደሚታሰበው የነፃነት ፀደይ የገቡም መስሏቸዋል። ነገርግን ሌላ አዲስ ጠላት ተተካባቸው። ከኮሚኒዝም የባሰ አስቀያሚና እና ደም አፍሳሽ ነበር። እርሱም በባልካን የቱርክ ሙስሊሞችና ቦስናክ ክርስትያኖች መኃል ተከስቶ ያለፈን የግጭት ታሪክ ቁርሾ የወረሰና እርሱኑ መነሻ አድርጎ ኢስላምን ከዩጎዝላቪያ ከስሩ ነቅሎ የማጥፋት ከንቱ ምኞት የነበረው  የሰርብ ፋሺዝም ነበር። አውሮፓውያኑ ለሰርብ ሸፍቶች በማበር ሙስሊሞች የተወረረች አገራቸውን ለመከላከል የሚያስችላቸውን መሳሪያ ሸያጭ አንኳ ከለከሉ። ሙስሊሞች ስር የማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደባቸው ጥቂት የአውሮፓ መሪዎች አውሮፓ ውስጥ ኢስላማዊት አገር የመገኘቷን አደገኝነትና ስጋት ይናገሩ ነበር !

ዓሊ ዒዘት ታዲያ ህዝባቸውን ይዘው በሞትና ሕይወት መኃል ዘመቻውን መሩ። የዘር ማጥፋቱ ተግባር ከአሳማሚ መስዋዕትነት፣ ሰበርኔስታና መሰል ቦታዎች ላይ የደም ባህር ከጎረፈ በኋላ በቦስንያ ነፃነት ተጠናቀቀ።

ዓሊ ዒዘት የበታችነትን የምትጠላ እና የጥበብ ዘውድ የደፋች ነፍስ ባለቤት ነበሩ። እስር ቤት ውስጥ ለማታለያዎች እና ማስፈራሪያዎች እንዳልታለሉት፤ ከእስር ውጪም ችግርና መከራን ታግሰዋል። በዕውቀትና ተግባር፣ በአስተሳሰብና ግብን አጥብቆ  በመያዝ የተካኑ

ሰው ናቸው። ብልህና አስተዋይ ሲሆኑ ጀግነነትም መለያቸው ነበር። ጀግንነታቸው ግን ከብልህነታቸው እንደሚበልጥ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

“ጀግንነት በጣም የጠፋና ብርቅ ስለሆነ ሕዝብ ከብልህነት ይልቅ ለርሱ ያዜማል።”

የግዙፍ ልቦና ባለቤቱ ዓሊዒዘት ሲፋለሙ የነበሩት ፈተና ሲጠናቀቅ እጅግ የሚጠሏቸውን አካላት እንኳ ቂም አልያዙባቸውም። “እኔ ዘንድ ጥላቻ ሳይሆን ምሬት ነው ያለው።” እና “አንድንም ሰው አሳንሼ ያየሁበትን አጋጣሚ አላስታውስም።” ሲሉ ስለራሳቸው ፅፈዋል። ፍትሕን እንደ በቀል ሳይሆን የነገራትን ወደ ቦታቸው መመለስ አድርገው ነበር የሚያዩት። ከይቅርታና ማለፍ ጋር በደልን ከተበዳዮች ያስወግዳሉ። ይህን አስመልክተው “በደል ላይ ድልን የመቀዳጀት ብቸኛው መንገድ ይቅርታ ነው። የፍትህ እርምጃስ ሌላ አዲስ በደል አይደለምን? “ ይላሉ።

ዓሊ ዒዘት በዚህ ሰፊ አስተሳሰብና ግዙፍ ልቦና ህዝባቸውን ከዓለም ዕይታና ጆሮ ስር ነቅሎ ለመጣል አሰፍስፎ የነበረውን አረመኔ ስልጣኔ አሸንፈውታል።

## ነፃነት ናፋቂው እስረኛ

ዓሊ ዒዘት ለሰው ልጅ የሰብዓዊነት አስኳል ነው ብለው የሚያስቡትን እና ደግሞም የሆነውን ነፃነት ናፋቂ ነበሩ።

በተመሳሳይ አምባገነንነትን የሰው ልጅ ጠንካራው ጠላቱ እንደሆነም ያምናሉ። ቁሳዊ ሃይል ሊቀማው የማይችለው የሰው ልጅ የማሰብ መብት የነጻነት ምንጩና የሰውነት ስሪቱ ኃይል መነሻው ነው ብለው ያስባሉ። በኮሚኒዝም እስር ቤት ሳሉ ስለራሳቸው እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል፡-"ንግግር ባልችልም ማሰብ ግን ችያለሁ። ይህን ችሎታዬን ፍሬ እስኪፈራ ድረስ እስከመጨረሻው ለመጠቀም ወሰንኩ።" ይላሉ።

የኮሚኒዝም ስርዓት ባለስልጣናት ዓሊ ዒዘት ከኢስላም መርሆችና ከነፃነት ትግል አቋማቸው በተወሰነ መልኩ በድርድር መኃል መንገድ እንዲመጡላቸው የማባበል ስራን ሰርተዋል። ከዓሊ ዒዘት ግን እምቢተኝነትና መናቅን እንጂ አላገኙም። እስር ቤት ሳሉ በሚደብቁት የዲያሪ ደብተር የሚከተለውን አስፍረዋል፡- "1987 ፌብሯሪ 27 ቀለል ያለ እንቅስቃሴ ያለበት ቀን ነበር። በጠዋቱ ወደ እስር ቤቱ አስተዳደር አስጠሩኝ። እስረኛን የመጠየቂያ ሰዓት ስላልነበር ትንሽ ጨነቀኝ። ግለሰቦች የግል ጉዳያቸውን በሚወያዩበት ክፍል ለይላንና ሳቢናን (ሴት ልጆቻቸው መሆናቸው ልብ ይሏል) ፈገግ ብለው እየጠበቁኝ አገኘኋቸው።

በደስታ ፊት የተቀበሉብኝ ምክንያቱ የመጡት ምንም ክፉ ነገር እንዳልተፈጠረ ለመሳየት ነበር። በቦስኒያ ሪፐብሊክ አስተዳደር የምህረት አድራጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ ለሆነው ኒኮላ ስቶያኖቪች የምህረት ይግባኝ ተብሎ እኔ እንድፈታ ሐሳብ መቅረቡን ነገሩኝ። ይህን ሂደት ያሳለጠውና ይግባኙን የፃፈው ደግሞ በወቅቱ

የኮሚቴው ፀሐፊ የለይላ የትምህርት ቤት ጓደኛ የነበረው ዘድራፍኮ ነበር። ሙሉ ፅሁፉን አነበብኩት። አልፈረምኩበትም። እስሩም ቀጠለ።” ይላሉ።

በይግባኙ ደብዳቤ እነርሱ የፈለጉት ዓሊ ዒዘት አሳሪያቸውን ይቅርታ እንዲጠይቁ፣ ፖለቲካዊና ሕዝባዊ ጉዳዮችን ትተው ቤታቸው እንዲቀመጡ የሚጠይቅ ነበር። ዓሊ በእምቢተኝነታቸው ቀጠሉ። ከዚህ ክስተት በኋላ በእስር ሁለት ዓመታትን አሳለፉ።

የእስር ቤት ፈተና ብዙ አስተምሯቸዋል። አስረኛ ሆነው የሚመጡላቸውን ወርቃማ የውልብታ እሳቤዎች ይፅፉ ነበር። ፅሁፋቸውን ከአሳሪዎቻቸውም እይታ ይሰውሩታል።

ከዚያ በኋላ እነዚህ የውልብታ ሐሳቦች ተሰብስበው “ሁሩቢ ኢለል ሑሪያ” (ወደ ነፃነት ሽሽቴ) በተሰኘ መፅሐፍ ተሰድሮ ተሰራጨ። ይህ ድርሳን ስር ሰደድ ኢማንን፣ ስል እሳቤን፣ ለሕይወት እና ፈተናዎቿ የጠለቀ ግንዛቤን አመላካች ነው። በዚህ መድብል ከተቀመጠ ውልብታ ውስጥ “እስር ቤት እጅግ አሳማሚ ነው አስኪባል ድረስ እውቀትን ይቸራል።” “የሰው ልጅ በእስር ቤት በቦታ አለመመቸት ቢሰቃይም በጊዜ ኃብት ግን ይትረፈረፋል።” የሚል ይገኝበታል።

## የሰብዓዊነት ተልዕኮ ተሸካሚ

ዓሊ ዒዘት ቢጎቪች በሰብዓዊነት አድማስ ልክ በተሰፋ መልኩ ጥልቅ ኢስላሚስት ነበሩ። የሰውን ልጅ ባህልና ዕውቀት በሙሉ ለማወቅ ንባባቸው ሰፊና ጥልቅ ነበር። በፍልስፍና፣ኃይማኖቶች፣ ሕግ፣ ታሪክና ስነ-ጽሁፍ እና ስዕል የተካኑ ነበሩ። የመፅሐፍቶቻቸውን ግርጌ፣ እይታና ውልብታዎቻቸውን ላጤነ አንባቢ በምስራቁና ምዕራቡ ዓለም ንባብ የዳበረ፣ ያነበበውን የሚተች የልከኛ መንገድ ህሊና ባለቤት መሆናቸውን አመላካች እንደሆኑ ይረዳል። መስመር ያልያዙ የመረጃዎች ጥርቅም ለተሸካሚው ኃላፊነት እንጂ የማዕረግ ስም ነው ብለው አያስቡም። ይህን አስመልክተው "ግነት የበዛበት የእውቀት ስያሜ የፈጠራ ችሎታን ይገድላል። ... የሰው ልጅ በብዙ ዘርፎች ያለምንም ስርዓትና ራዕይ የዕውቀት ባለቤት ሊሆን ይችላል። ብዙዎቹ ልሂቃን የእውነተኛ እውቀትን ምንነት ሳያውቁ ኖረው አልፈዋል።" ይላል።

ዓሊ ዒዘት በኢስላማዊና ሰብዓዊ አስተሳሰብ ረገድ በመፅሐፍቶቻቸው ግዙፍ አስተዋፅዖን አበርክተዋል። እጅግ ጎልተው ከሚታወቁት ውስጥ "ኢስላም በምስራቅ እና ምዕራብ መኃል" "ወደ ነጻነት ሽሽቴ" እና "የኢስላም ምንነት" ይጠቀሳሉ።

ኢስላም ዛሬ ላይ በሕመም እየተሰቃየ ላለው የሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ ሰብዓዊ ተልዕኮ ህክምና እንደሆነ ጥልቅ እምነታቸው

ነው። ኢስላም በባህሪው የሰውን ልጅ የዕይታ አድማስ በሸፈነው የታወረ ቁሳዊነትና ከሕይወት ፍልሚያ ተሸንፎ በሚያፈገፍገው መንፈሳዊነት መኃል ሚዛናዊ መንገድን አስቀምጧል። ኢስላም የሰውን ልጅ ምንነት ለሁለት የሚገምስ ሳይሆን ማብቂያ ያለውን ተጨባጩን እና የሌለውን አድማሱን አጣጥሞ የሚወስድለት "ሶስተኛው መንገድ" ነው። ተጨባጭ መንፈሳዊነት ዋነኛው የኢስላም ምልክት ነው። ዓሊ ዒዘት እንደሚያስቡት በኢስላም ውስጥ ምሉዕ የሚሰኘው ሰው ቅዱስ አይደልም።

እንደውም ጠንካራና ተጨባጭ አማኝ ማህበራዊ ተልዕኮውንና የሕይወት ሚናውን በሚገባ የሚወጣ ነው። ዓሊ ዒዘት እንደሚሉት ለኢስላም ያለን ግንዛቤ የተስተካከለ ቢሆን ኖሮ ተግባራዊና በተጨባጩ ዓለም የሚኳዝ ሰው ከቅዱስ የበለጠ ነው። ጥብቅ የሆኑት መላዕክት ለተሳሳቹ አደም ይሰግዱ ዘንድ የታዘዙበት ሚስጥርም ይኸው ነው።

የስልጣኔን አረመኔነት ለኢስላም ባላቸው ፅኑ ኢማን እና ሰብዓዊ እሳቤ አሸናፊ ለሆኑት ዓሊ ዒዘት ቢጎቪች አላህ ይዘንላቸው።

# 6

# ሙሐመድ አሰድ

*(የኢብራሒምን ፍኖት አሳሹ)*

በረዥሙ የሙሐመድ አሰድ የሕይወት ልምድና የበለፀገ መንፈሳዊ ጉዞ ውስጥ እጅግ ወሳኙ የኢብራሒምን (ዐሰ) ፍኖት በመፈለግ ሂደት ሳለ፤ በኢስላም ጠለል ላይ ታሪክ ሳይሸፍነው እንዲሁም የጊዜ እጅ ሳይጫወትበት ማግኘት መቻሉ ጉልሁ ነው። ቀጥሎም በቁም ነገር የተሞላውን ረዥሙን ዕድሜውን የኢስላምን ተልዕኮ ተሸክሞ ለኡማው የገባውን ቃሉን ሞልቶ ማለፉ ነው።

ሙሐመድ አሰድ በወቅቱ የኦስትሪያ ኢምፓየር ግዛት አንድ ክፍል በነበረችው ዩክሬን ውስጥ በሉምበርግ አውራጃ በ1900 ተወለደ። ወላጆቹ ሊዮፖልድ ዋይስ ብለው ሰየሙት። ኢስላምን እስከተቀበለበት ጊዜ ድረስ በዚሁ ስም ነበር የሚጠራው። ቤተሰቡ በኦሪትና ተልሙድ አስተምህሮ የታወቀ አይሁዳዊ ዘር ሲሆን ከቅድመ አያቶቹም ውስጥ በአይሁድ እምነት ጥልቅ ዕውቀት የነበራቸው መነኮሳት ነበሩ። አሰድ በልጅነቱ ከኃይማኖተኛ ቤተሰቡ የጠበቀ ልምድ መሰረት የአይሁድ እምነትን፣ የሒብሪውና አረማይክ ቋንቋዎችን በጥልቀት ተማረ። ታዳጊ እያለ ወደ ቪየና ተዘዋውሮ ስነ-ፅሁፍና ፍልስፍናን ተማረ። ዕድሜው ሃያዎቹ እንደሆነ ወደ በርሊን በማቅናት በጀርመን አንዱ ጋዜጣ ላይ በጋዜጠኝነት ሙያ ተቀጥሮ መስራት ጀመረ።

በ1922 አሰድ ፍልስጤም ያለ አጎቱን ለመጎብኘት ተጓዘ። እዚያው እያለም ሰፊ ሽፋንና ስርጭት ላለው የፍራንክፈርተር ዚቶንግ ጋዜጣ ሪፖርተር ሆኖ መፃፍ ጀመረ። ይህ ስራ በምስራቁ ዓረብ ውስጥ የመንቀሳቀስ ዕድልን ሰጠው። ለምዕራቡ የምስራቅን ማሕበራዊ ሕይወትና የባህል ድልብ ማሳየት ጀመረ። በ1924 ከፊል ፅሁፎቹ በአንድ ላይ ተሰብስበው “ሮማንቲክ ያልሆነው ምስራቁ” በሚል መድብል ወጥቷል። ይህ መድብል እኔ እስከማውቀው ድረስ ወደ ዓረብኛ አልተተረጎመም።

ሙሐመድ ፍልስጤም ውስጥ እያለ የኢብራሒምን (ዐሰ) ፍኖት እና የውርስ ቅሪት መፈለግ ጀመረ። አውሮፓዊ አይሁድ ከመሆኑ

ጋር ወደ ፍልስጤም በተሰደዱት የአውሮፓ አይሁዶች እና በአገር ባለቤቶቹ በቁድስ ዓረብ ነዋሪያን መኃል ያለውን የላቀ ልዩነት አስተውሏል። በጥንታዊቷ የቁድስ ጎዳናዎች የሰዎቹን ፊት በማንበብና እና ሕይወታቸውን በማጤን የኢብራሒምን (ዐሰ) ስብዕና በዓረቦቹ ፊት፣ ባህሪና ቁመና ላይ አካል ለብሶ እንዳገኘው ፅፏል። እውነተኛ የኢብራሒም ልጆች ናቸው። ወራሪዎቹ የአውሮፓ አይሁድ ዘሮቹን ግን ለአገሪቱ አዲስ እንግዳ ሆነው አይቷቸዋል። በእርግጥ በእነርሱና በኢብራሒም (ዐሰ) መኃል የነበረው ግንኙነት ከረዥም ክፍለዘመናት በፊት ነትቧል። አሰድ ፍልስጤም እና ግብፅ የቆየባቸው እነዚያ ዓመታት ስለ ምስራቁ ዓረቢያ ዕውቀትንና እስከ መጨረሻው አብሮት የነበረውን ዓረብን መውደድ ባህሪ ችሮታል።

## ጉዞ ወደ መካ

በአይሁዳዊ ቤተሰቡ ውስጥ ስር የሰደደ ኃይማኖታዊ ውርስ ከመኖሩ ጋር የሙሐመድ አሰድ ሰብዓዊና ፈጣን መንፈስ ከጠባቡ የአይሁድ እምነት ጋር ተጣጥሞ ሊሄድለት አልቻለም። አይሁዶች የበሰበሱበትን የዘራቸውን የበላይነት ለማሳለጥ ኃይማኖትን ከፊት ሆነው እየመሩት እንደሆነ አስተዋለ። ሌላው ቀርቶ (ከእሳቤያቸው የላቀው) የፍጥረተ ዓለሙ አስገኚ ህላዌ ፅንሰ-ሐሳብ በባህላቸው ወደ ሙሉ ዘረኛ አምላክነት ተቀየረ።

በአይሁዶች እምነትና እውቀት መሰረት አምላክ "ከሰው ልጅ ውስጥ የዕብራውያን ሕዝቦች ጉዳይ ብቻ ነው የሚያሳስበው።" የሚል ይገኝበታል። እንደውም በሙሐመድ አሰድ እይታ የፍጥረተ ዓለሙ አምላክ እነርሱ ዘንድ "ሌሎች ፍጥረታትን ያስገኘው የአንድን የተመረጠ ሕዝብ ፍላጎት ለማሳለጥ ስለሆነ ኀሰኛ ነበር።"

በአይሁድ እምነት ውስጥ በነገሰው ጠባብ የዘረኛ አስተሳሰብ አለመርካቱ አሰድን ኢስላም ውስጥ ስላለው የሕይወት ትርጉምና በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ሰብዓዊ መርሆችን ወደ ማጥናት የወሰዱት መግፍኤዎች የሆኑት።

1926 አሰድ በርሊን ሳለ የሱረቱ ተካሱርን ትርጉም አነበበ። ኢስላም ልቡ ውስጥ ገባ። ምዕራፏን ካነበበ በኋላ አግራሞቱን እንዲህ አስፍሮታል፡-"ይህ ባለፋት ምዕተ ዓመታት በዓረቢያ ባህረ-ገብ የኖረ ሰው ጥበብ አይደለም። የቁርአን ድምፀት የሙሐመድ ድምፀት ከመሆን የላቀ ነው።" ብሏል። አሰድ ኢስላምን እንደተቀበለ አብራው ኢስላምን ከተቀበለቺው የመጀመሪያ ሚስቱ ኤልሳ ጋር ወደ ሐጅ ተጓዘ። ኤልሳ የሐጅ ስርዓትን መጠናቀቅ ተከትሎ ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ አኼራ ሄደች። አሰድ ግን በእምነት ወንድሞቹ መኃል መቆየትንና ልቡን የወሰደውን እምነት ለመርዳት፣ መርጦ የመጣበትን ኡማ ዳግም ከፍ ለማድረግ ሊታገል አስቦ እዛው መቆየትን ወሰነ።

የሙሐመድ አሰድ ኢስላምን መቀበል በጭፍን ተከታይነት ወይም በምስራቁ ሮማንሲ በመሳብ የምዕራቡ ታሪክ ድንገት ጭልም ስላለበት አልነበረም። ሲጀምር አሰድ ሮማንቲክ ሰው አልነበረም። ለዚህ ነው ስለ ምስራቁ የፃፈው የመጀመሪያ ድርሳኑ “ሮማንቲክ ያልሆነው ምስራቁ” በሚል ርዕስ የሆነው። ይልቁንም አሰድ የሕይወትን ትርጉም እና ተፈጥሯዊ ትሩፋቷን የሚያስስ ብልህ ሰው ነበር። ይህንንም በኢስላም ፍኖት ውስጥ አገኘው። በጥልቀትም አመነበት። የርሱ ኢስላምን መቀበል የሕይወትን ትርጉምና ውስጣዊ ይዘት በማወቅ ላይ የተመሰረተ የብልህ ሰው ሕሊና ውሳኔ ነበር።

ይህን አስመልክቶ አሰድ “እኔ ኢስላምን የተቀበልኩት በሙስሊሞች መኃል ረዥም ጊዜ ስለኖርኩ አይደለም። ጉዳዩ ከዚህ ተቃራኒ ነው። በመኃላቸው ለመኖር የወሰንኩት ኢስላምን ስለተቀበልኩ ነው።” ሲል ጽፏል። (The Road to Mecca ገፅ 20)

ሙሐመድ አሰድ በዚህ መልኩ በዓረቢያ ባህረ-ገብ ለስድስት ዓመታት ኖሮ የዓረብኛ ቋንቋ ችሎታውን አበለፀገ። በኢስላማዊ ባህል ውስጥ ሰመጠ። The Road to Mecca (ጉዞ ወደ መካ) በተሰኘ መፅሐፉ መስህብ ባለው ብዕሩ የበረሃ ጉዞ ማስታወሻውን አስፍሯል። አሰድ ከንጉስ ሱዑድ ቢን ዓብዱልዐዚዝ እና በወቅቱ ልዑል ከነበረው ንጉስ ፈይሰል ጋር ተዋወቀ። ሙኒራ የተሰኘችውን ሳዑዲያዊቷን ባለቤቱንም አገባ። ዛሬ ላይ በኒዮርክ ዩኒቨርሲቲ

ታዋቂውን የአንትሮፖሎጂ ምሁር ጠላል ቢን አሰድንም ወለደችለት።

## አሰድ ከበረሃው አንበሳ ጋር

የሙሐመድ አሰድን ጠንካራና ጥልቅ እምነት እንዲሁም ስብዕና ከሚያሳዩ፤ ልብን ሰቅዘው ከሚይዙ ህያው ምስክርነቶች መኃል በዘመናችን የሙጃሂዶችን ቁንጮ ሸይኽ ዑመር አል-ሙኽታርን ለማግኘት ከሒጃዝ (መካ) ወደ ሊቢያ ያደረገው አስቸጋሪ፣ ስጋት እና አደጋ የተሞላበትን ጉዞ ማድረጉ አንዱ ነበር። አሰድ ሒጃዝ በነበረበት ወቅት ከስደተኛው የሰይኑሲ ሸይኽ አሕመድ ሸሪፍ ጋር ተዋወቀ። የአሰድ ቀልብ የሸይኹ እስረኛ ሆነ። አሰድ ስለ ሰኑሲ እንዲህ ሲል ፅፏል፡- “በዓረቢያን ፔኒንዙላ ሙሉ እንደ ሰይድ አሕመድ የወደድኩት ስብዕና የለም። ምክንያቱም እንደሳቸው ለላቀ ግብ ሲል ነፍሱን ሙሉ በሙሉ መስዋዕት ያደረገ አንድ ሰው ስለሌለ ነው። ከአገር የተባረሩ ስለሆኑ ከሰላሳ ዓመታት ፍልሚያ በኋላ ወደ አገራቸው የመመለስ ጉጉት ፊታቸው ላይ ይታያል። በሰሜን አፍሪካ የወራሪዎቹን ገዢዎች እንቅልፍ ያሳጣ ስም ነው....” ይላል። (The Road to Mecca ገፅ 253-254)

ሸይኽ ሸሪፍ አህመድ ሰኑሲ ሙሐመድ አሰድ ወደ ሊቢያ ተጉዞ ሸይኽ ዑመር አል-ሙኽታርን እና የጂሃድ እንቅስቃሴያቸውን በቅርበት ድባቡን አይቶ፣ እንቅስቀሴው የሚጠናከርበትን ዕቅድና ዕይታ ሰጥቶ ይመጣ ዘንድ ፈለጉ።

አሰድ የዚህን ግብዣ የላቀ ዓላማ አስቦ ሳያቅማማ ተቀበለ። የሸይኽ ዑመር አል-ሙኽታር ወታደሮች ልክ እንደ መጀመሪያው የሶሐባ ትውልድ ለነፃነትና ኢስላማዊ ሕይወት እንደሚጋደሉ ፅፏል፡- “ውጤቱ ምንም ይሁን በመራር ትግል ውስጥ ለነበረቺው ለዚያች ቡድን እኔ የሐሳብ እገዛ ማድረጌ ልክ እንደ ሶላት ግዴታዬ የምቆጥረው ነበር።” ይላል።(The Road to Mecca ገፅ 268)

ቀይ ባህርን ከእንጨት በተሰራች ጀልባ ስጋት ከተሞላበት፣ የግብፅና ሊቢያን አቃጣይ የበረሃ ጉዞ ካቋረጠ በኋላ ከሸይኽ ዑመር አል-ሙኽታ ጋር ታሪካዊ ግንኙነታቸው እውን ሆነ። አሰድ እንዲህ ይስለዋል፡- “ብዙም ሳይቆይ ዑመር አል-ሙኽታር ኮቴው በጨርቅ የተጠቀለለ አነስ ያለ ፈረስ ጋልበው መጡ። በሁሉም አቅጣጫ ሁለት ሁለት ሰዎች ያጀቧቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ከኋላቸው ተከትለዋቸዋል። የምንጠብቅባቸው ቋጥኝ ዘንድ ሲደርሱ አንዱ ባልደረባቸው ከፈረሱ ይወርዱ ዘንድ አገዛቸው። ስለሚያነክሱ በግድ እንደሚራመዱ አስተዋልኩ። ሳንገናኝ በግምት ከአስር ቀናት በፊት በነበረ አንድ ፍልሚያ ላይ ቆስለው እንደሆነ አወቅኩኝ። በምታንፀባርቀው የጨረቃ ብርሃን ታግዤ በግልፅ አያቸው ጀመር። መካከለኛ ቁመት ከጠንካራ አቋም ጋር ያላቸው ሰው ናቸው። ፂማቸው ልክ እንደበረዶ ነጭ ሆኖ አጭር ነው። ሐሳብ የሰፈረበት ፊታቸው ጥልቅ መስመሮች አሉት። ዓይኖቻቸው ወደ ውስጥ የገቡ ሲሆኑ ስርጉዳቸውን ያስተዋለ ማንም ሰው ከዚህ ከባድ የትግል ሕይወት ውጪ ቢሆኑ ኖሮ ዓይኖቻቸው ሳቂታና እና ተንቀልቃይ

ውበት እንዳላቸው በቀላሉ ያውቃል። አሁን ግን የበደል ህመም የወለደውን የጀግንነት ቁጥርት የያዙ ናቸው።" (The Road to Mecca ገፅ 275)

የሰኑሲና የአሰድ ሐሳብ ሊቢያ ውስጥ ከፍራ የተሰኘ ክልል ውስጥ ብቻ መሰረቱን ያደረገውን የጂሃድ እንቅስቀሴ ወደ ሌላውም ማስፋትና ከግብፅ የገንዘብና መሳሪያ እርዳታ ምንጭ ማድረግ ነበር። ሆኖም አሰድ ሊቢያ ሲደርስ ከፍራ ክልል በፋሺስቶቹ እጅ ስር ወድቃለች። በግብጽና ሊቢያ ድንበር ላይም ከፍተኛ የቁጥጥር ኬላ አድርገዋል። ውይይታቸው ፍሬ ባያፈራም ሙሐመድ አሰድ ከሸይኽ ዑመር አል-ሙኽታር ጋር ሁለት ቀናት የፈጀ የጂሃድ እንቅስቀሴውን የመታደግ እስትራቴጂዎች ሲለዋወጡ ቆዩ። ሸይኹ ጥንካሬያቸውን ባይፈታተነውም፣ ቆራጥነታቸውን ባያሸረሸረውም ቅሉ የጂሃድ እንቅስቃሴያቸው እያበቃለት እንደሆነ የተረዱ ይመስሉ ነበር። ሸይኹ ለጎብኚያቸው አሰድ "ልጄ ሆይ እኛ የሕይወት ቆይታችን ማብቂያ ድንበር ላይ ነን። ወራሪዎቹን እስከናስወጣ ወይም እስክንሞት እየተጋደልን ያለነው ስለ እምነታችን እና ነፃነታችን ነው። ከዚህ ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም። እኛ ለአላህ ነን ወደርሱም ተመላሾች ነን።" አሉት።(The Road to Mecca ገፅ 277)

አሰድ ሊቢያ ውስጥ ያለው ወታደራዊ ፍልሚያ በርሱ እይታ አከሳሪ መሆኑን ሲገነዘብ ሸይኽ ዑመር አል-ሙኽታር ከርሱ ጋር ሆነው ወደ ግብፅ እንዲያፈገፍጉና ሕይወታቸውን እንዲታደጉ፣ እዛም

ሆነው የሊቢያውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ አብረው ዳግም ለመገንባት፣ በወቅቱ ግብፅን የወረሩት እንግሊዞች ጣሊያን ጋር ያላቸውን የሻከረ ግንኙነት እንደ እድል ተጠቅመው የመስራት ሐሳብ አቀረበላቸው። ሸይኽ ዑመር ግን ከሙጃሂድ ተከታዮቻቸው ጋር ሊቢያ ውስጥ ሆነው ጉዳያቸው ድል እስኪያደርግ ወይም ለርሷ መሞት አለብኝ በሚለው ሐሳባቸው ላይ ፀኑ።

አሰድ በመጣበት መንገድ መመለስ ግዴታ ሆነበት። የመልስ ጉዞው ግን በአበባ የተነጠፈ አልነበረም። እጅግ ፈታኝ፣ በጣሊያን ጥበቃና የፍተሻ እሾሃማ አጥር ስር ማቋረጥ ነበረበት። የጣሊያን የፍተሻ ቡድን ከዑመር አል-ሙኽታር ሙጃሂዶች ጋር አገኙት። የተኩስ ልውውጥና ፍልሚያም ተካሄደ። በፍልሚያው ሜዳ አምስቱ ሰማዕት ከሆኑ በኋላ ያንን መንገድ ማቋረጥ ቻሉ። ከዚህ ትግል ከሞላው ጉብኝት ስምንት ወራት በኋላ ዑመር አል-ሙኽታር በፋሽስት ጣሊያን ስርዓት ስቅላት ሰማዕት ሊሆኑ ተማረኩ።

## ወደ ኢስላማዊው ምዕራብ ምልሰት

አሰድ በጀዚረተል ዓረብ እና ሰሜን አፍሪካ ኢስላምን ለመርዳት ውድ ዋጋ ከከፈለ በኋላ ሙስሊሞችን ለማገዝ በሚል ወደ ህንድ ክፍለ አህጉር ፊቱን አዞረ። ኢስላማዊውን ምስራቅ ክፍል ጎበኘ። ኢራንን፣ ከመለያየታቸው በፊት አፍጋኒስታንን እና ህንድንም ጎበኛቸው። ገጣሚና ፈላስፋውን፣ የኢስላምን ጉዳይ አጥብቆ የያዘውንና የአስተሳሰብ ምጥቀቱን ከተረዳው ሙሐመድ ኢቅባል

ጋር በአካል ተገናኙ። ኢቅባል ለወደፊት የምትመጣውን የኢስላማዊት ግዛት (ፓኪስታን ሪፐብሊክ) አስተሳሰባዊ መሰረት በማስቀመጡ ላይ አጋዥ እንዲሆነው እዛው እንዲቆይ አሳመነው። (The Road to Mecca ገፅ 14)

ሙሐመድ ኢቅባል ከሞተ እና ፓኪስታን ከተመሰረተች በኋላ አሰድ ዜግነቷን አገኘ። በኢስላማዊ መነቃቃት አስተዳደር ውስጥም ሰራ። ለአገሪቱ መጪ ጊዜ ኢስላማዊ መተዳደሪያዋ ምን መሆን እንዳለበት እሳቤውን አኖረ። እነዚህ እሳቤዎች "ሚንሃጁል ሁክም ፊል ኢስላም" በተሰኘው መጽሐፉ ወስጥ የሰፈሩ ፅንሰ-ሐሳቦች ናቸው።

አሰድ ከዚህ ቀጥሎ በፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ውስጥ የፓኪስታን የዓረቡ ዓለም ግንኙነት ሃላፊ ሆኖ ሰራ። ቀጥሎ ደግሞ ኒዮርክ በሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ ልዩ አምባሳደሯ ሆነ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ቀናት ሚስጥራቸውን እንደተናገሩት ከሆነ እስራኤላውያን አሰድ ኒዮርክ ውስጥ በሃምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የፓኪስታን አምባሳደር ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ከፉ ጥርጣሬን ጠርጥረውትና አይሁዳዊ ዳራውን በመጠቀም ለረከሰ ጉዳያቸው ሊጠቀሙት አስበው የማማለል ሙከራ አድርገው ነበር። በመጨረሻ ግን ያገኙት መልስ ሰውየው የማንነቱን ገመድ ከነርሱ ቆርጦ ለኢስላም መግመዱን ነበር። ለመታለልና እርሱን ለመጠቀም ምቹ ስብዕናም አልነበረም።

በ1952 ሙሐመድ አሰድ “ዘ ሮድ ቱ መካ” የተሰኘው መፅሐፉን ለመፃፍና ሰፋ ያለ ጊዜ ለማግኘት ሲል በተባበሩት መንግስታት የፓኪስታን አምባሳደርነቱን በገዛ ፍቃዱ ለቀቀ። ያንን መፅሐፍ ያበረከተችልን ስራ መልቀቅ ምንኛ የተባረከች ናት!

ሙሐመድ አሰድ የቀረው ዕድሜውን በሕይወቱ ትልቅ የሚባለውን ፕሮጀክት አንገቱን ደፍቶ ለመስራትና ለመኖር ከአሜሪካዊት ባለቤቱ በላ/ሐሚዳ ጋር በ1955 ወደ አገረ-ስፔን አቀና። ያ ፕሮጀክት የላቀውን ቅዱሱን ቁርአን ወደ እንግሊዝኛ መተርጎም ነበር። The Message of The Qura’n “የቁርአን መልዕክት” በተሰኘው ድርሳኑ ያሳካው ትርጉም ነው። የፀሐፊውን የዕውቀት ስፋት በሚያሳዩ የግርጌ ማስታወሻዎች፣የቁርአንን ውስጠ-ትርጉም፣ የዓረብኛን ቋንቋ ሚስጥር በጥልቀት በመረዳት የተሰራ ነው። በዋሺንግተን የአሜሪካ ኢስላማዊ ግንኙነት ኮሚቴ (Council on American-Islamic Relations /CAIR/) ይህን የትርጉም ስራ እንደ እስታንዳርድ ተቀብሎና መሰረት አድርጎ ሚሊዮን የቁርአንን ትርጉም በማዳረስ ዘመቻው ውስጥ ዛሬም ድረስ ያከፋፍለዋል።

አሰድ ዘጠናዎችን ከተሻገረ እና ረዥም ዕድሜን ከኖረ በኋላ በ1992 ወደ ላይኛው ዓለም ሄደ። የዕድሜውን ፀደይ የተገኘበት አህጉር አውሮፓ ውስጥ ኖሮ አስከሬኑም በአንደሉስ የኢስላማዊ ስልጣኔ ቅሪት ባለባት ግራናዳ ነበር የተቀበረው። በ2008 የቪየና ክፍለ ከተማ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሕንፃ ትይዩ ያለውን ዋና አውራ ጎዳናዋን “ሙሐመድ አሰድ” ስትል ሰይማለች። በምስራቁና

ምዕራቡ መኃል ድልድይ ለመገንባት የለፉ፣ የዓለም ዜጋ እና የቁርጥ ቀን ልጇ አድርጋ ወስዳዋለች።

## ተላምደው ባንድ የኖሩ

ሙሐመድ አሰድ በአውሮፓውያን ስልጣኔና ዕውቀት ውስጥ የሰው ልጅ ማንነት በመንፈስና ቁስ ይከፈላል የሚል እሳቤ አለ ብሎ አያምንም። ሁኔታው በጀላለዲን አር-ሩሚ ስንኞች የሚገለፅ ይመስላል፡-

በመንፈስ ገላዬ የለም ግርዶ
ባንድ ላይ ኖሩ በተላምዶ።

በ20ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ አካባቢ አውሮፓ ውስጥ ሰፍኖ የነበረው የዘረኝነትና ጥላቻ መንፈስ በጀርመን ናዚ እንቅስቃሴ ተቋጭቷል ብሎም አያምንም። ለነዚህ ሁለት በሽታዎች ታዲያ መድሃኒት መፈለግ ጀመረ። ኢስላምን ለሰው ልጅ “የሁለት ማንነቶች አንድነት” እና “የሰብዓውያን ወንድማማችነት” መንገድ ሆኖ አገኘው። ወደ እምነቱ የመሳቡ ሚስጥርም ይኸው ነበር።

በ20ኛው ክፍለዘመን መግቢያ አካባቢ አሰድ ኢስላማዊውን መንፈስ በተደራጀ መልኩ ማግኘት የጀመረው በምስራቁ የኢስላም አገራት ዘጋቢ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ነበር። በምስራቁ ክፍል ሲኖር ያደረበትን ተፅዕኖ እንዲህ ከትቦታል፡- “አውሮፓ ውስጥ ከቁሳዊው የውክቢያ ሕይወት አንፃር፤መጀመሪያ አካባቢ ነፍሴ

ውስጥ እጅግ የተረጋጋ ሕይወትን የማግኘት ፍላጎትና ጉጉት ተፈጠረ። ይህ ዝንባሌ የልዩነቱን መነሻዎች ወደ መመልከት መራኝ። በዚህ መልኩ በኢስላም አስተምህሮት ላይ በልዩ ሁኔታ ትኩረት የማደርግ ሰው ሆንኩኝ። በወቅቱ ዝንባሌዬ ወደ ኢስላም ማህደር መሳቤን በበቂ ሁኔታ የሚያናግር ግን አልነበረም። ሆኖም ፊትለፊቴ በተቻለ አቅም የሰው ልጅ ሕይወቱን ከውስጣዊ ግጭት በፀዳ መልኩ ስርዓት ለማስያዝ፣ ለማደራጀት፣ የላቀ ወንድማዊ ስሜትን ለማስፈን አዲስ ዕይታን ግን ይዣለሁ።" (Islam at the Cross Road ገፅ 16)

አሰድ በዓመታት ንጉደትና በምስራቁ ዕውቀት ስር ከሰደደ በኋላ በኢስላም ውስጥ እስከዛሬ የሚያስሰውን የፈጣሪን አንድነትና የሰው ልጅን እኩልነት አገኘ። "ኢስላም የሰውን ልጅ ወደ ሁሉም የሕይወት አቅጣጫዎች በአንድነት ይዞት ይነጉዳል።" (Islam at the Cross Road ገፅ 102) "ኢስላም የስነ-ምግባርና ተግባር፣ ግለሰባዊና ማሕበራዊ ስርዓት ነው።" (Islam at the Cross Road ገፅ 97) የሚለውንም ተረዳ።

የኢስላማዊ አምልኮ ተግባራትን አስኳል ይዞት ሲያስተነትን ሙሐመድ አሰድ ከመንፈሳዊ ጥራትና ማህበራዊ ስርዓት እሳቤዎች በልዩ ሁኔታ የተሰሩ ሆነው አግኝቷቸዋል። "አምልኮን በተመለከተ ኢስላማዊው እሳቤ ሶላትን ብቻ ያጠቃለለ አይደለም። ይልቁንም ሕይወት የተባለን በሙሉ ያካተተ ፅንሰ ሐሳብ ነው። ዋና ግቡም

በእያንዳንዱ ሰው ላይ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ማንነቶችን ማስገኘት ነው።" (Islam at the Cross Road ገፅ 106)

ከኢስላም ልዩ ባህሪያት፣ ከጥንካሬው ምንጭ እና ከዘል ዓለማዊነቱ ሚስጥር ውስጥ ይህ አንዱ ነው ፡-"ይህ በሰው ልጅ ሕይወት የስነ-ምግባር እና ቁሳዊ ማንነቶች ምሉዕነት ነው። ኢስላም የትም ይሁን መች የተቆጣጣሪነት ኃይሉ ምክንያትም ነው። የሰው ልጆችን ለመምራት በእጃቸው ምሪትን የያዙት ነብያችን ለሰው ልጅ ሕይወት የሚጠበቡት በመንፈስና ቁስ በሚገለፁት ሁለቱም አቅጣጫዎች ነበር።" (Islam at the Cross Road ገፅ 90)

ሙሐመድ አሰድ አውሮፓ ውስጥ በብሄርተኞች ሲጣስ ያየው ሰብዓዊ ወንድማማችነት በኢስላም ውስጥ ተከብሮ አይቶታል። "በኢስላሙ ዓለም ያለው ውስጣዊ ጥንካሬና ማህበራዊ ትስስር ዓለም ለማህበረሰብ ስርዓት ከሞከረው ማንኛውም ስርዓት የተሻለ ነው።" ይላል። (Islam at the Cross Road ገፅ 39)

የትኛውም ጥንታዊ ስልጣኔ እንደ ኢስላም ሕብረ-ብሔራዊነትን ያወቀም ይሁን ያፀደቀ የለም።

ይህ ደግሞ እንደ አሰድ ላለው የሮማውያንና ግሪክ ስልጣኔዎች ታሪክ ትጉ የጥናት ሰው የሚደበቅ ጉዳይ አልነበረም።

## የሙስሊሙ ዓለም ንቃት

ሙሐመድ አሰድ በውስጡ ከተሸከመው ሁነኛ እሳቤ አንዱ በሙስሊሙ ዓለም የመንፈስ እና አስተሳሰብ ተሐድሶ ነው። ለዚህም ሁለት መፅሐፍቱን መድቧል። Islam at the Coss Road (ኢስላም በመንታ መንገድ ላይ) እና ሚንሃጁል ኢስላም ፊል ሁክም የሚሉት ናቸው። በመፅሐፍቱ " ከሸሪዓ ላይ ለዘመናት የተጠራቀሙና የተከመሩ ልማዳዊ የአተረጓጎም ትብታብ ክምሮችን ማራገፍ ይኖርብናል።" ይላል (Islam at the Cross Road ገፅ 118)።

አሰድ በኢስላማዊው ማዕከል የሰፈነውን ጭፍን ተከታይነት፣ የህሊና መሳነፍ እና ለዳግም መነቃቃት እንዲሁም ተሐድሶ ምንም አስተዋፅኦ አለማድረጉን ይኮንናል። ምክንያቱም "በእውነታው የአዕምሮ መስነፍ ከአካል ስንፍና አያንስም።" ይላል። (Islam at the Cross Road ገፅ 107)

በተጨማሪም አሰድ የምዕራቡን ዓለም ትምህርት የተማሩ እና ያልበሰሉ፣ ጊዜንና ቦታን ባላማከለ መልኩ የምዕራባውያኑን አስተምህሮ ዩኒቨርሳል መመዘኛ ያደረጉ ክሱራንንም ይኮንናል። በእርግጥ አሰድ "የየህዝቡ ባህላዊ ልዩነትና የአቀባበል እይታ መለያየት፣ እውነታዎች የሚቀርቡበት መንገድ እንጂ ዕውቀት በራሱ ምዕራባዊና ምስራቃዊ አይደለም።" ሲል ያስጠነቅቃል።

ራሳቸውን ምዕራባዊ ለማድረግ የሚውተረተሩትን ሰዎች ወጥሮ የያዘበት አንዱ መንገድ እነርሱ የኢስላምን ምጡቅ ተልዕኮና ዘውታሪነቱን አለመረዳታቸውን ነው። “ከፊል የቁርአን አናቅፅ ወሕይ ሲወርድ የነበሩ ህዝቦች ላይ ያተኮረ እንጂ በዚህ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ለሚኖሩ ዘመናዊ ሰዎች አይደሉም የሚለው አስተሳሰብ ሙስጠፋ (ሰዐወ) የቆሙበትን ነብያዊ ብርሃን ማሳነስ ነው።” ይላል። (Islam at the Cross Road ገፅ 90-91)

በአሰድ ዕይታ እነዚህ ሰዎች ወደዚህ ደካማ አቋም ያደረሳቸው ምስጢር በራስ አለመተማመን እና ራስን ካለማክበር ጉድለት የመጣ ነው። ይልቁንም “ሙስሊም ራሱን ቀጥ፣ኢስላምን ሕያው አድርጎ መኖር ይችላል።” ይላል። (Islam at the Cross Road ገፅ 85) በተጨማሪም “አንድ ስልጣኔ ወይም ባህል ከኪሳራዋ በኋላ ዳግም ልታብብና ወደ መኖር ልትመጣ የምትችለው በራሷ ስትገረምና ካለፈ ታሪኳ ጋር ባላት መልካም ግንኙነት ነው።” ብሎም ያስባል። (Islam at the Cross Road ገፅ 86)

በምስራቁም ይሁን ምዕራቡ አስተሳሰብ የመጠቀው አሰድ የሰው ልጅ ምን ያህል በስልጣኔ ማማ ላይ ቢሰቀል አንኳ ኢስላም ውስጥ በቂ መልስ እና ሁነኛውን ህክምና ያገኛል ይላል፡- “ስለዚህ የሰው ልጅ አሁን ያለበት መሻሻልና ዕድገት ከኢስላም ተብቃቅቶ የሚቆምበት ሁኔታ ላይ ለመሆኑ የሚያሳይ ምልክት አይደለም። ይልቁንም ኢስላም ካመጣው ስነ-ምግባራዊ ስርዓት የተሻለ

መፍጠር አይችልም።” ይላል። (Islam at the Cross Road ገፅ 114)

በኢብራሂም ፍኖት አሳሹ ሙሐመድ አሰድ ላይ የአላህ እዝነት ይስፈን !

# 7

# ሙሐመድ ሐሚደላህ

*(ለዕውቀት የመነኑ መናክሴ)*

ዶክተር ሙሐመድ ሐሚደላህ በኩሩ ነፍስ፣ በጥልቅ ዕውቀት በትጉና ረቂቅ ልቦና ረዥም ዕድሜን ኖረዋል። የምድራዊ ኑሮን ብልጭልጭ ትተው፣ በመማርና ማስተማር ተጠምደውና ኢስላምን በማገልገል አልፈዋል። ልኬት የለለው፣ ከባህር የሰፋ የሁለንተናዊ ዕውቀት ባለቤት፤ ዱንያ ምንም የማታጓጓቸው ዛሂድና አላህን የማምለክ ተምሳሌት ሰው ነበሩ።

ደቡብ ሕንድ ሃይደራባድ ከተማ በ1908 ተወለዱ። የቤተሰባቸው ስረ-መሰረት ወደ ቁረይሽ የዘለቀ ነው። ቤተሰቡ በቀድሞው ጊዜ

ከሒጃዝ የሐጃጅ ቢን ዩሱፍን ጭቆና ሸሽቶ የተሰደደ ሲሆን ከስምንተኛው ዓ.ሂ ጀምሮ ዘሩ እዛው ተተከለ። ከዚህ ምርጥ ዛፍ ላይ ትላልቅ ዳኞች፣ የአገር መሪዎች እና ሕንድ ኢስላማዊ ስርዓት በነበራት ወቅት ከተራራ የገዘፉ ዝናቸው የናኘ የልሂቃን ቅርንጫፎች ተግኝተውበታል። ከመጨረሻዎቹ ታዲያ የዶክተር ሐሚደላህ ታላቅ ወንድም እና ወደ ኡርዱኛ ቋንቋ የበላዘሪን "አንሳቡል አሽራፍ" የተረጎሙት ሸይኽ ሐቢበሏህ እንዲሁም "የነወዊን ሶሂህ ሙስሊም ሸርሕ" ወደ ኡርዱኛ የተረጎሙት ታላቅ እህታቸው ሸይኻ አመተል ዓዚዝ ይጠቀሳሉ።

## የማይረካ የዕውቀት ጥማት

የሙሐመድ ሐሚደላህ የዕውቀት ጥምና ፍላጎት ድንበርን አያውቅም ነበር። ሁለት ሰርተፊኬት፣ ሁለት ማስተርስ፣ ሁለት ዶክትሬት ያላቸው ሲሆን በአጠቃላይ 20 ቋንቋዎችን ተምረዋል። ከነዚህ ውስጥ ዐረብኛ፣ ኡርዱኛ፣ ፔሪሺያኛ፣ ቱርከኛ፣ ላቲን፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ጣልያንኛ፣ ሩሲያኛ፣ ዴንማርከኛ፣ ስዊድንኛ እና ፊንላንድኛ ይገኙበታል። ዕድሜያቸው ሰማንያን እንደተሻገረ የተማሩት የመጨረሻ ቋንቋ ታይላንድኛ ነበር። የሁለተኛው ዓለም ጦርነት እንቅፋት ባይሆንባቸው ኖሮ ከዚህ ሁሉ ዶክትሬት በኋላም ተጨማሪ ፒኤችዲ ያገኙበት የነበረው ከሞስኮ ዩኒቨርሲቲ የሩሲያኛ ቋንቋ ነበር።

ወደ መዲነቱል ሙነወራ በማቅናት የቁራኦች ሸይኽ ከሆኑት ሐሰን ቢን ኢብራሒም ዘንድ በመማር ሐሚደላህ ዘንድ ውድና ልባቸው ላይ ልዩ ቦታ ያለውን የቁርአን አል-ከሪምን ኢጃዛ ወሰዱ።

ሸይኽ ሙሐመድ ሐሚደላህ የመጀመሪያውን ኢስላማዊ ትምህርታቸውን በዳረል ዑሉም ሸርቂያ በኡርዱ ቋንቋ ነበር የተከታተሉት። ዓረብኛ፣ እንግሊዝኛ እና ፋርስኛን እዛው ነው በደንብ የተማሩት። በ1919 ህንድ ውስጥ በኢስላማዊ ዕውቀት ስሩ የጠለቀ ታሪክ ባለው መድረሰቱ ኒዟሚያ ተቋም በመግባት 1923 ላይ ተመረቁ። ከዓመት በኋላ ደግሞ አሚር ዑስማን ዓሊ ኻን ሒያድርባር ውስጥ በ1918 ባቋቋመው ዩኒቨርሲቲ ገብተው ሁለተኛ ላይሰንሳቸውን ዕድሜያቸው ገና ሃያዎቹ ሳለ በ1928 አግኝተዋል።

ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ ሁለት ማስተርሶችን የተጎናፀፉ ሲሆን የመጀመሪያው በኢስላማዊ ጥናት እና ሁለተኛው ደግሞ በዓለማቀፍ ህግ ነበር። በ1932 የዑስማን ዩኒቨርሲቲ ቀለም ተማሪዋን ወደ ቱርክ፣ ግብፅ፣ ሶሪያና ሳዑዲ በመላክ የጥንት ኢስላማዊ መዛግብትን ያገላብጥ ዘንድ አደረገች።

ኢስታንቡል በነበሩበት ወቅት ጀርመናዊው ኦሬንታሊስት ፍሬዝ ኮርኒኮ ቦን ዩኒቨርሲቲ ገብተው ከፍተኛ ትምህርታቸውን ያጠናቅቁ ዘንድ ሁኔታዎችን አመቻቸላቸው። ዶክትሬታቸውን ጨረሱ። ለሁለት ዓመታትም እዛው ዐረብኛ እና ኡርዱኛ ቋንቋዎችን አስተማሩ። በ1934 ፈረንሳይ ሰርቦን ዩኒቨርሲቲ ገብተው ሁለተኛ

ዶክትሬታቸውን "በነብያዊው እና ኹለፋኡ አር-ራሺዲን ወቅት የነበረ ኢስላማዊ ዲፕሎማሲ" በሚል ርዕስ የጥናት ፅሁፍ አቅርበው አጠናቀቁ።

ሙሐመድ ሐሚደላህ በ1935 ሰፊ ዕውቀት፣ ዓለማቀፍ ግንዛቤና የሕይወት ልምድ ይዘው ወደ ሃይድራባድ ተመለሱ። በዑስማን ዩኒቨርሲቲ በኢስላማዊ ጥናት ፋካልቲ መምህር እና እስከ 1948 መግቢያ ድረስ የህግ ዲፓርትመንት ኃላፊ ሆነው ሰሩ።

## ኩሩ እና አምቢተኛ ነፍስ

ሙሐመድ ሐሚደሏህ ኢስላማዊቷ የሃይድራባድ ኤሚሬት ከሕንድ አገር ተገንጥላ ራሷን የቻለች ግዛት እንድትሆን ሐሳቡን በደንብ ከሚደግፉት ውስጥ አንዱ ነበሩ። ምክንያቱም ይህቺ ግዛት በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ የላቀ ታሪካዊ ሚና ስላላት ነው። በሕንድ ክፍለ አህጉር ላይ በኢስላማዊ ስልጣኔ ከፈኩ ማዕከላት አንዷ ስለነበረች እና በዚያው ኢስላማዊ ማማ ላይ ሆና እንድትቆይ አጥብቀው ይፈልጉ ስለነበርም ጭምር ነው።

በ1948 ሕንድ ከብሪታኒያ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ከወጣች በኋላ የዚህችን ኤምሬት ነፃነትና መገንጠል ዕውቅና ከሚሰጠው ዲፕሎማሲያዊ የልዑካን ቡድን ጋር አብረው ወደ ተባበሩት መንግስታት ድርጅት አቅንተዋል። የሕንድ ጦር ግዛቲቱን ሲያወድምና የዲፕሎማሲ ቡድኑ የነፃነት ዕውቅናው ጥያቄ ሳይሳካለት ሲቀር ሙሐመድ ሐሚደሏህ ከዚያች ጊዜ ጀምሮ እግራቸው የሕንድን ምድር

ላትረግጥ እምቢኝ አሉ። ዓለም ላይ እንደዛ እየዞሩ እንኳ ውሳኔያቸውን ዕድሜ ልካቸውን ጠብቀው አልፈዋል።

ሐሚደሏህ ፈረንሳይ ውስጥ ሆነው ሃይደራባዲያዊ ዜግነታቸውን እንደጠበቁ ግማሽ ምዕተ-ዓመት ያህል የሚሆን (1948-1996) ኖረዋል። ከፈረንሳይ መንግሰት እና ከብዙ ኢስላማዊ አገራት የዜግነት ግብዣ ቀርቦላቸው ከፍ ባለ የነፍስ ክብር እና ደባ የተፈፀመባትን አገራቸውን ሃይደራባድን በፍፁም ታምነዋት ውድቅ አድርገዋል።

ፈረንሳይ ውስጥ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል በመኖሪያ ፍቃድ ብቻ ነበር የኖሩት።

ሐሚደሏህ ፈረንሳይን ትተው የሄዱት ዕድሜ ካደከማቸው፣ሁሌም ኢስላምን ለማገልገል ቀጣይነት ባለው ምርምር እና ስራ ዕድሜያቸውን አሟጠው ከጨረሱ በኋላ ነበር።

አሜሪካ የምትኖር የወንድማቸው ልጅ የሆነቺው ሰዲዳ ዓጣኡሏህ ለጤናቸው ክትትል ስትል፣ ስለደከሙና ዕድሜያቸው ስለሄደ በቅርበት እንድተከታተላቸው በማሰብ ወደርሷ እንዲመጡ አጥብቃ ለመነቻቸው። በ1996 የአክብሮት ጥያቄዋን ተቀበሏት። ከኋላቸው ሊረሱና ሊጠፉ የማይችሉ ትዝታዎችን እንዲሁም ፋናቸውን አኑረው በ2002 ከዚህች ዱንያ የተረጋጋች ነፍስን ይዘው እስከወጡበት ጊዜ፤ በፍሎሪዳ ግዛት ጃክሶንቪል ከተማ የዕድሜያቸውን የመጨረሻ ዓመታት ከርሷ ጋር አሳለፉ።

አዛኟና ትሁቷ የወንድማቸው ልጅ ሰዒዳ ዓጣኡላህ Impact International ላይ ባሰፈረቺው የሐዘን መግለጫ ፅሁፏ ለርሷ ካላቸው እዝነት የተነሳ እንደሚከተለው ይቀልዱት እንደነበር ይህን አስፍራለች፡- “የሞት መላዕክን በቻልኩት አቅም አንቺ ባለሺበት ነፍሴን እንዳያወጣት እደራደረዋለሁ።” አላህ ምኞታቸውን አሳካለቸው። ረፋድ ላይ እርሷ ቤት በሌለችበት ወደ አኼራ ሄዱ።

## በዛሂዶች ጎዳና

ሙሐመድ ሐሚደሏህ አላህን አምላኪ፣ ተናናሽ፣ ትሁት እና የእዝነት ክንፋቸውን ዝቅ አድራጊ ነበሩ።

ፈረንሳይ በሰርቦን ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው ከሙስሊም ወጣቶች ጋር ትምህርታዊ የካምፕ ጉዞ ወጥተው በእጆቻቸው የምግብ ሳህን ያጥቡ፣ ዓዋቂና ታዋቂ ከመሆናቸው ጋር መሬት ላይ አብረውም ይቀመጡ ነበር። በሕንድ ክፍለ አህጉር ከታዋቂ የትምህርት ማዕከላት አንዱ ወደሆነው “ዳረል-ሙሶኒፊን” ሁሌም ሲገቡ ባዶ እግራቸውን ሁነው ነበር። ይህን ሲያብራሩ የመልዕክተኛው (ሰዐወ) ሲራ ወደተፃፈበት ክፍል ጫማ ለብሶ መግባትን ይጠየፉ ስለነበር ነው። ለማለት የፈለጉት በሰባት ጥራዝ የተዘጋጀውን የሱለይማን አን-ነደዊን የሲራ ድርሳን ነው። ሲበዛ ዛሂድ እና ራሳቸውን ፈታሽ ነበሩ። ሌላው ቀርቶ ለንጉስ ፈይሰል ሽልማት ሲታጩ “እኔ የፃፍኩት ለአላህ ስል ብቻ ነው። ዲኔን አታበላሹብኝ።” ሲሉ ውድቅ አድርገውታል።

## በዕውቀት ምኩራብ ውስጥ መቋረጥ

ዶክተር ሙሐመድ ሐሚደላህ መፅሐፍትን በብዛት በማዘጋጀት ከሚቆጠሩ ጥቂት ዑለሞች ተርታ የሚሰለፉ ናቸው። ለነገሩ ረዥም ዕድሜያቸውን በዕውቀትና በፅሁፍ ምርምር ነው ያሳለፉት። ሌላው ቀርቶ አላገቡም ነበር። ሐሚደላህ ብዙ አስርት ጥራዞችን ፅፈዋል፣ አርትኦትም ሰርተዋል።

- በቁርአን ፕሮጀክታቸው ውስጥ ወደ ፈረንሳይኛ ታሪኩንና አስተምህሮቱን በተመለከተ ሰፋ ያለ ሐተታ ካስፈሩበት በኋላ ተርጉመዋል። ወደዚህ ቋንቋ ከተተረጎሙ ቅጂዎች የዚህኛውን ያህል ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጠው የለም።

  የሐሚደላህ ትርጉም ታዋቂ እና ፈረንሳይ፣ ካናዳና ምዕራብ አፍሪካ በሚገኙ የቋንቋው ተናጋሪዎች ዘንድ ተመራጭ መሆን ቻለ። የፈህድ የቁርአን ህትመት ህብረትም እርሱን ተመርኩዞ በብዛት አትሞ አሰራጭቶታል።

- በከቡሩ የሐዲስ ሳይንስ ዘርፍ ደግሞ በ101 ሂ ያለፈውን የኃማም ቢን ሙነቢህ አስ-ሶንዓኒን ድርሳን ከአቡ ሁረይራ (ረዐ) ከዘገበው የነብዩ (ሰዐወ) ሐዲስ ላይ ሐሚደላህ ግርዶሽን ገፈዋል። ሐሚደላህ በዚህ ስራቸው ላይ በሶሐቦች ዘመን የነብዩ (ሰዐወ) ሐዲስ መሰነድ አልጀመረም ከሚለው የተሰራጨ ዕይታ በተቃራኒ በሱና እና ሰነድ ታሪክ ላይ እምነት የሚጨምር ስራን አበርክተዋል። ኦሬንታሊስቶች ለሶሂሕ አል

ቡኻሪ በሰሩት ትርጉም ዙሪያ ክፍተቶችን ከማዳላት በፀዳ አዕምሮ እና በተጋ ልብ መፅሐፍ አዘጋጅተውበታል።

- በነብያዊው ሲራ ዘርፍ ሙሐመድ ሐሚደላህ የኢብኑ ኢስሐቅን (151ሂ ያለፉ) ስራ ማረጋገጫ ሰርተውለታል። ሰዎች ከርሱ በኋላ የተፃፈውን የኢብኑ ሒሻምን (213 ሂ ያለፉ) የሲራ መፅሐፍ ብቻ በመጠቀም ችላ ብለውት የነበረ ሲሆን ይህን የጥንት ድርሳን ወደ ኢስላማዊ አካዳሚ ማህደር አጠቃለውታል።
- በኢስላማዊ ፖለቲካ ህገ-ፍልስፍና ዘርፍ ውስጥ ብዛት ያላቸው መፅሃፍትን ያበረከቱ ሲሆን ጎልተው የሚታወቁት ግን 3 ናቸው።

እነዚህ መፅሐፍት በነብያዊው እና ቅን ምትኮቻቸው ዘመነ-አስተዳደር የነበሩ የፖለቲካዊ ሰነድ ስበስቦች ናቸው። ሰነዶቹ ማንኛውም የኢስላማዊ ፖለቲካ ተመራማሪ፣ በሙስሊሞችና ሙስሊም ባልሆኑ አካላት መኃል ፖለቲካዊ ትስስርን መሰረት ማስያዝ የሚሻ አካል ሊጠቀማቸው የሚችሉ ውድ ድልብና ኦሪጂናል ሰነዶች ናቸው። የሐሚደላህ ሁለተኛ መፅሐፉቸው The First Written-Constitution in the World የሚል ሲሆን በመልክተኛው (ሰዐወ) ዘመን በመዲና ለመጀመሪያ ጊዜ የተፃፈውን ህገ መንግስት፣ የገዢ ተገዢ ግንኙነት በውዴታና መፃፃፍ ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት እና ስለ መንግስታዊ ግንባታ ሂደት ኢስላም ማህበራዊ ውልን እንዴት

ያየዋል የሚለውን ዳጎስ ካለ መቅድም ጋር ወደ እንግሊዝኛ መተርጎምና ማቅረብ ነበር። ሶስተኛ ልዩ የጥናት ስራቸው ርዕሱ “የሮማውያን ህግ በኢስላማዊ ፊቅህ ላይ ተፅዕኖ ነበረውን?” የሚል ነበር። በዚህ ጥናታቸው የኢስላማዊውን ፊቅህ ኦሪጂናሊቲ አብራተዋል። ስረ-መሰረቱ የሮማውያን ህግ ነው ብለው ግምታዊ ሐሳብ ለሚሰጡት ኦሬንታሊስቶች አፍ የሚያስይዝ መልስ ሰጥተውበታል።

– የዐረብኛ ጥንታዊ መዛግብትን በመፈተሸ ዘርፍ ሐሚደላህ ብዙ የሰሩ ሲሆን ከነርሱ ውስጥ የሙሐመድ አሽ-ሸይባኒን “አስ-ሲየሩል ከቢር”፣ የዋቂዲን “ኪታቡ አር-ሪዳ”፣ የበላዚሪን “አንሳቡል አሽራፍ”፣ የቁተይቢን “ኪታቡል አንዋእ”....ወዘተ እና ሌሎችንም ሰርተዋል።

የአላህ እዝነት በዕውቀቱ መነኩሴ ሙሐመድ ሐሚደላህ ላይ ይስፈን።

ደግ ነገሮች በመልካም ፀጋዎቹ ለሚሟሉት አላህ ምስጋና የተገባው ነው።

*** ተፈጸመ ***




ይህ መፅሐፍ ዶ/ር ሙሐመድ ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢ በ20ኛው ክ/ዘመን የነበሩ ሙስሊም ነቢባንን የአስተሳሰብ ፍሬ፣ የሕይወት ስረትና አኑረው ያለፉትን አሻራ አጠር ባለ መልኩ በእምቅ ይዘት የዳሰሱበት ድርሳን ነው። ኢስላምን ከተለያየ ምንጩ የጠጡ፤ የተገኙበት መሬት የተለያየ ግን የሐሳባቸው መሽከርከሪያ አንድ የሆኑ ስብዕናዎች ናቸው። ኢስላም እኛ በሳልነው ቅርፅ መልኩ ብቻ እንዳልሆነ እና ምናልባትም እነርሱ ካቆሙበት ላይ የሚጀምረው የዛሬው ትውልድ አዕምሮው ውስጥ ሌላ የአስተሳሰብ አቅጣጫን መፈተሸና ማስተናገድ የሚያስችል ዝግጅት ይኖረው ዘንድ ታሪክና ፋናቸው መንገድ ጠራጊ ነው ብዬ አምናለሁ።

ሙስሊሞች ወደ ዓለም የመሪነት እና ተግባራዊ ተምሳሌትነት መድረክ ዳግም ይሰየሙ ዘንድ አያሌ የተሐድሶ ተጣሪያን የአስተሳሰብ ትምህርት ቤት መስርተውና ታግለው አልፈዋል። ሌሎች ደግሞ የእሳቤ መንገድ ፍተሻ፣ የዘመንን ዘውግ ያማከለ በኢስላማዊ እውቀት ስርጭት ውስጥ የአረዳድ ደርዝን ለመጠበቅ የካሪኩለም እጦትን ለመቅረፍ የለፉና ሐሳብ ያቀረቡም ነበሩ። ይህን ድርሰት ወደ አገርኛ ለመመለስ ያነሳሳኝ ሁነኛ ምክንያቴም የኢትዮ ሙስሊም ከመስጂድ እና ግለሰባዊ ኃይማኖተኝነት በዘለለ ስለ አካባቢው፣አገሩ እና ዓለም ጉዳይ ይመለከተኛል የሚልን ሐሳብ ምርኩዝ አድርጎ ወደ አበርክቶ ይነሳ ዘንድ ነው። ለእርምትና አስተያየት ሁሌም ዝግጁ ነኝ።

ወንድማችሁ
ዐብዱራህማን ሰዒድ(ሜጢ)
ረመዷን 1441/ ሚያዚያ 2012 ዓ.ል

አሳታሚ
الوسطية للنشر والتوزيع
Al-Wasatiyyah Publishing